# ቀቢጾች

## ከጋብሮቮ ምድር

በኣረፈዓይኔ ሓጎስ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

All Rights Reserved

# ለቀልዶቹ እንደ መንደርደሪያ

ቱርኮች የቦልካንን ባሕረ-ገብ መሬት ባስገበሩበት ወቅት ቡልጋሪያዊቷ፣ ወይዘሮ በዝሃና ልጆቿን ይዛ ከቬሊኮ ቱርኖቫ (የቡልጋሪያ ርዕሰ ከተማ) እንደተሰደደች አፈ-ታሪክ ይናገራል:: ከቡልጋሪያዊቷ ልጆች አንደኛው ራቾ ይባል ነበር:: ቀጥቃጩ ራቾ የሰፈረውም በድንጋያማው ያንትራ ወንዝ ዳርቻ ነበር:: ራቾ የቆረቆራት መንደር ባሁኑ ጊዜ ጋብሮቮ ትባላለች:: ለቆርቋሪዋ ራቾ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ፣ የጋብሮቮን ከተማ ሰንጥቆ እሚያልፈው ያንትራ ወንዝ መኻል ባለች ደሴት ላይ ሐውልት ቆሞለታል:: ቀልደኞቹ ጋብሮቮዎች ሐውልቱ ስለቆመበት ስፍራ ሲያወሱ፣ «ምንም አይነት አገልግሎት ሊሰጥ የማይችል ቦታ ነው» ይላሉ::

የጋብሮቮ ምድር ጭንጫነት የተወላጆቹን ሕይወት እጅግ ድካም የበዛበትና መራራ አድርጎት ነበር:: ለዚህም ሳይሆን አይቀርም፣ ጋብሮቯውያን ታታሪዎች፣ የፈጠራ ሰዎችና ቀልደኞች ለመሆን የበቁት::

በዚች መፅሐፍ ውስጥ የተሰበሰቡት ቀልዶች ጋብሮቯውያን ብልህና የፈጠራ ችሎታ ያላቸው፣ በቁጠባ የሚኖሩ ጥንቁቅ ሕዝቦች መሆናቸውን ያረጋግጥልናል:: ይሁን እንጂ ቀብቃቦች፣ ቆንቋኖች የሚሏቸውም አይታጡም:: ያም ሆነ ይህ የነገን መኖር የተገነዘቡ

ቆጣቢዎችና አስተዋዮች መሆናቸውን የሚክድ የለም።

ጋብሮቮ፣ ባሁኑ ወቅት የተለያዩ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማፍራት ከሚታወቁት ግንባር-ቀደም የቡልጋሪያ አውራጃዎች አንዷ ናት። ይህም ሆኖ የጋብሮቮ ተወላጆች በክረምት ወራት ድመቶቻቸው ወደ ቤት ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ቤት ውስጥ የተጠራቀመውን ሙቀት እንዳይስወጡ ጭራዎቻቸውን ይቆርጡዋቸዋል ይባላል። ከዚህ አነጋገር በመነሳት ይመስላል፣ ጭራ ቆራጣ ድመት በየሁለት አመት አንዴ ለሚካሄደው አለማቀፋዊ የቀልድና ምፀት ሥነ ጥበባዊ ውድድር፣ እንዲሁም ለቀልዶችና ምፀቶች ፌስቲቫል አርማ ሆና የምታገለግለው።

ይህ ዓለማቀፋዊ የምፀትና ቀልድ ውድድር ባያዝነው አመት ለሰባተኛ ጊዜ ተካሂዷል። የውድድሩ ሥነ ሥርዓት የሚካሄደው፣ ጋብሮቮ ከተማ በሚገኘው ባለሦስት ፎቅ የቀልድና ምፀት ማዕከል ውስጥ ነው። ማዕከሉ የተቋቋመው በ1963 ሲሆን፣ ሥራውን ከጀመረ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ በዩኔስኮ ሊታወቅ ችሏል። ባጭሩ የጋብሮቮ ምድር ዓለማቀፋዊ የቀልድ ማዕከል በመሆን ላይ ትገኛለች።

ጋብሮቭዎያን አስቂኝና ልዩ ፍጡሮች በመሆናቸውም ይህ ችሎታቸው የሚያስደንቅ ላይሆን ይችላል። ይህን መፅሐፍ ያነበበ ግን በጋብሮቭዎያን ቀልድ መርካቱና መዝናናቱ የማይቀር ነው። ለዚህም ነው መፅሐፉ በእንግሊዝኛ፣ ሩስያንኛ፣ ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ ተተርጉሞ በዓለም ተሰራጭቶ የሚገኘው።



## የጋብሮቮ ሕዝብ ብዛት

ጋብሮቮን በመጎብኘት ላይ ያለ ቱሪስት አንዱን ጋብሮቮ አዛውንት የአካባቢውን ሕዝብ ብዛት ቢጠይቃቸው፣ «ቁጥራቸው ምንም ያክል ቢሆን ሁሉም ጋብሮቮ ናቸው፣ ልጄ!» አሉት ይባላል።

* * *

## ትርፉ ሲቀልጥ

ጋብሮቮን ሲጎበኙ የሰነበቱ ቱሪስት፣ ማስታወሻ ሊገዙ ወደንዱ ሱቅ ገብተው ለየት ያለ ዕቃ ከመረጡ በኋላ፣ ዋጋውን ይጠይቁና ሳይከራከሩ የተጠየቁትን ከፍለው ይሄዳሉ።

ይሁንና፣ ከፍ ያለ ዋጋ ሳይጠይቅ መቅረቱ የቆጨው ባለሱቅ ቱሪስቱን አውራ ጎዳናው ድረስ ተከትሎ፣ «ይስሙ ጌታው! የገዙትን ዕቃ ይመልሱልኝ፣ ገንዘብዎን አልፈልግም» አላቸው ይባላል።

* * *


## ዶሮ ብታልም ጥሬዋን

አንዱ አግረኛ፣ «ስንት ሰንት ሆነ፣ ጌታው!» ሲል ጋብሮቮውን ይጠይቀዋል።

«አስር... ከኻያ አምስት ስቶቲንኪ.» በማለት ጋብሮቮውም ይመልሳል። (ስቶቲንኪ «ሳንቲም» ማለት ነው።)

## «ምሳ እንብላ»

ጓደኛሞች ተሰብሰበው እጋብሮቮው ቤት ካርታ ሲጫወቱ ያረፍዳሉ። የምሳ ሰዓት እንደተቃረበ ታድያ ባለቤትየው ከመቀመጫው ተነሳና፣ «ጨዋታውን እዚህ ላይ እናብቃና ሁላችንም ወደየቤታችን ሄደን ምሳችንን እንብላ» እላቸው ይባላል።



## ይከፍላላ!

ሦስት ጓደኛሞች ምግብ ሊበሉ ሆቴል ይገቡና ሁለቱ እጃቸውን ሲታጠቡ፣ ጋብሮቮው ውድ የሆኑትን የምግብ አይነቶች ከዝርዝሩ ላይ በፍጥነት ይሰርዝ ጀመር።

የሆቴሉ ባለቤት፣ በድርጊቱ ተገርመው አፍጠው ሲመለከቱትም «ሂሳቡን የምከፍለው እኔ ነኝ!» አላቸው።

* * *



## ለካስ...

ዶክተር ወዳጁን እመንገድ ዳር ያገኘ ጋብሮቮ፣ ሕመሜን የሚያስታግስልኝን መድኃኒት ቢነግረኝ በማለት፣ «ዶክተር፣ ጉንፋን ሲይዝዎ ምን ያደርጋሉ?» ብሎ ቢጠይቀው፣ «እስላለኋ፣ ወዳጄ!» ሲል መለሰለት - ለካስ እሱም ጋብሮቮ ኖሯል!!

* * *

## ጠቃሚ ትምህርት

ቀድሞ የነበረበትን እዳ ያልከፈለው የእያ ማንዮ ጉረቤት ሁለተኛ ብድር ሊጠይቅ ይሄዳል። ሽማግሌው ማንዮም በትሕትና ተቀብለውት ችግሩን ካዳመጡ በኋላ፣ እፊት ለፊቱ ያለውን ጠረጴዛ እየመለከቱ ከመሳቢያው ውስጥ የሚፈልገውን ያህል ገንዘብ እንዲወስድ ይፈቅዱለታል።

ባለ እዳው መሳቢያውን ይጐረጉርና «እያ ማንዮ! ለምን ይቀልዱብኛል? መሳቢያው ውስጥ ሰባራ ሳንቲም እንኳ የለም'ኮ!» ይላቸዋል።

ይኸኔ አዛውንቱ ማንዮ፣ «እዬ ልጄ፣ የመጀመሪያውን እዳህን ሳትከፍል እንዴት ሰባራ ሳንቲም እኔ ዘንድ ሊኖር ይችላል ብለህ ነው?» ሲሉ መለሱለት።

* * *

## ቀለበት በፈረቃ

«ቀለበትህን የት ጣልከው ጃል?»

«አልጣልኩትም እባክህ:: ባ.የዝነው ሳምንት ቀለበቱን የማድረጉ ተራ የባለቤቴ ስለሆነ እርሷ ዘንድ ነው::»



## ብልሁ ማንኛቸው ነው?

ጋብሮቮው ርካሽ አልቤርጎ ተከራይቶ ተኝቷል:: ይሁንና እኩለ ሌሊት ገደማ፣ የቱኋኖቹ ምጥመጣ አላስተኛ ይለዋል:: ይኸኔ አጅሬ መብራቱን ያበራና በሩን ከፍቶ ሲያበቃ ክፉኛ ወርውሮ ከዘጋው በኋላ ተመልሶ ይተኛል::

ደባሉ እጅግ ተረብሾ ኖሮ፣ «ምነው ጃል፣ በጤናህ ነው?» ሲል ጠየቀው::

«ደህና ነኝ፤ ብቻ ቱሃኖቹ ስላስቸገሩኝ የሄዱኩ



እንዲመስላቸው ብዬ ነው» አለው ይባላል::

* * *

## ቸሩ ጋብሮቮ

«ስማ አሳላፊ! አሥር ስቶቲንኪ ከምግብ ጠረጴዛው ሥር ወድቃለችና ካገኘሃት መልስልኝ:: ካጣሃት ግን ጉርሻ ትሁንህ» አለ አሉ ሥሌው ጋብሮቮ::

* * *

## መመካከሩ አይከፋም

ጋብሮቮውን የበሩ ማጠፊያ ይወልቅበትና በሩን ሊጠግን ይነሳል:: ልጁን ጠርቶም ከጐረቤት መጥረቢያ እንዲዋስ ይልከዋል:: ነገር ግን ልጅየው ባዶ እጁን ይመለሳል፤ ጐረቤትየው 'መጥረቢያ የሚባል ነገር የለኝም' ሲል ዋሽቶት ነበረና!

አባት መልሱን ሲሰማ እጅግ ተቆጥቶ፣ «ይህን ገብጋባ ዱሮውንስ መቼ አጣሁት! ሂድና የኛን መጥረቢያ ከዕቃ ቤት አምጣልኝ» አለ ይባላል::

## መስተንግዶ

ዘማች ጓደኛውን ከብዙ ዓመታት በኋላ ያገኘው ጋብሮቮ የሚኖርበትን ከተማ ሲያስጎበኘው አረፈደና፣ የምሳ ሰዓት እንደደረሰ አንድ ምግብ ቤት በርቀት እያመለከተው፣ «በል እንግዲህ ወዳጄ፣ እዚያ ቤት ጥሩ ምግብ በዝቅተኛ

ዋጋ ስለምታገኝ ወደዚያው አዝግም:: አንተ ምሳህን በልተህ እስክታበቃ እኔም አንዲት ጉዳይ ስላለችኝ ቤቴ ደርሼ እመለሳለሁ» አለው ይባላል::

* * *

## ሒሳብ፣ ሒሳብ ነው

ጋብሮቮው የአንድ ሌቭ (ብር) እዳ ነበረበት:: ታዲያ አበዳሪውም ጋብሮቮ ኖሮ አላስቆም አላስቀምጥ ይለዋል:: በየቀኑ መኖሪያ ቤቱ እየተመላለሰም እዳውን እንዲከፍል ይጨቀጭቀው ነበር:: እንግዲህ አበዳሪው በመጣ ቁጥር ባለእዳው ጋብሮቮ አንድ፤ አንድ ሲጋራ ይጋብዘው ነበር:: ታዲያ በአስረኛው ቀን አጅሬ ማስታወሻ ደብተሩን አውጥቶ የጋበዘውን ሲጋራ ሒሳብ ካሰላ በኋላ፤ «እዳዬ ይኸው ነው፣ ጌታው! አንተም እኔ ዘንድ ያጤስከው ሲጋራ አንድ ሌቭ ሞልቷልና ደህና ሰንብት!» ብሎ አሰናበተው::

* * *

## ሠራተኛ... እንደ ቻንድራ

ከእለታት አንድ ቀን የፋብሪካ ባለቤት የሆነ አንድ ጋብሮቮ ወደ ሕንድ አገር ይሄዳል:: እዚያ እንደደረሰም የሒንዱ አምላክ የሆነችው የቻንድራን መታሰቢያ ሐውልት ይመለከታል:: ስድስት እጆች ያሉትን የቤት ቅርፅ ያየው ጋብሮቮ ነጋዴ በቻንድራ እጆች ብዛት ስለተማረከ፣ ወደ



አስጐብኚው ዘወር ብሎ፣ «ለፋብሪካዬ መቅጠር የምፈልገው እንደሷ አይነት ሠራተኞችን ነው»አለ::

* * *

## ማን ማንን ሊበላ?

ጤንነት ያልተሰማቸው ጋብሮቮያዊቷ ወይዘሮ ቀድሞ የማያውቋቸውን ዶክተር እባቡር መንገድ ያገኟቸውና፣ «ዶክተር፣ ጤንነት አይሰማኝም:: እህል አይበላኝም፤ ያሆረኛል፣ እባክዎትን ይህን ሕመም የሚያስታግስልኝ መድኃኒት ይዘዙልኝ» ሲሉ ይለምኗቸዋል::

«እሜትዬ ልረዳዎት ዝግጁ ነኝ:: ብቻ ጥቂት ምርመራ ስለሚያስፈልግ ልብስዎን ማውለቅ ይኖርብዎታል» አሏቸው ጋብሮቮው ዶክተር::



## የፈሰሰ ብራንዲ ይታፈሳል!

«በዚህ ብርድ እመንገድ ዳር ምን ገተረህ ጃል?»

«ከግሮሰሪ የገዛሁት የብራንዲ ጠርሙስ ወድቆ ስለተሰበረብኝ፣ የፈሰሰው መጠጥ እንደ በረዶ ሲጋገርልኝ አንስቼ ለመውሰድ እየጠበቅሁ ነው።»

* * *

## ፍልሚያ

ሁለት ጋብሮቮዎች ይጣሉና ሊፋለሙ ይወስናሉ። ታዲያ ከተሜዎች እንዳይስቁባቸው የግጥሚያውን ቦታ ከከተማ ወጣ ያለ ስፍራ ሊያደርጉት ይስማሙና አውቶቡስ እንደተሳፈሩ፣ አንደኛው የደርሶ መልስ ቲኬት ሲያስቆርጥ፣ ሌላኛው የመሄጃውን ቲኬት (የአንድ ጉዞ ቲኬት) ብቻ ያስቆርጣል።

ይኸኔ የደርሶ መልስ ቲኬት ያስቆረጠው እየተኩራራ፣ «የመመለስ ተስፋህ የመነመነ መሆኑን ተገንዝበሃላ!» ቢለው፣

«ተሳስተሃል ወንድሜ፣ የመመለሻ ቲኬት ያልገዛሁት ባንተ ቲኬት እመለሳለሁ ብዬ ነው» አለው ይባላል።

* * *

## የፍቅር መግለጫ

«ፍቅሬ፣ ላንቺ ያለኝን ፍቅር ለመግለጥ ቃላት



ያጥሩኛል!»

«ቃላት ፍለጋ አትጠበብ፣ ወዳጄ! ቁጥሮችም ያገለግላሉ።» (ያለውን ንብረት ዋጋ፣ የገቢውን መጠን ማለቷ ነው።)

* * *

## ማስጠንቀቂያ

የጋብሮቮው ሚስት የቤቷን ግድግዳና ኮርኒስ ከጊዜ ወደጊዜ ኩላ እየቀባች ቤቷን በዕዳት ትጠብቅ ነበር። ይሁን እንጂ ባለቤቷ አንደዜ፣ «ግድግዳዎቹን መቀባትሽን ብትተዪ ይሻላል። ክፍሎቹ በጣም እየጠበቡ ናቸው» ብሎ ሲገስፃት ተሰምቷል።

* * *

## ስንተዋወቅ?

የሳይንስ ክፍለ-ጊዜ ነው። መምህሩ 'ሰልፈውሪክ አሲድ' ስለሚባለው የአሲድ አይነት በማስተማር ላይ ናቸው።

«ልጆች፣ አሁን ይህን የወርቅ እንክብል እዚህ አሲድ ውስጥ ልከተው ነው። እና አሲዱ ሳንቲሙን የሚያበላሸው ወይም የማያበላሸው መሆኑን ከናንተ መኻል አስቀድሞ ሊነግረኝ የሚችል አለ?»

«አያበላሸውም ቲቸር፣ ሲል አንዱ ተማሪ ተሽቀዳድሞ።

«ለምን?»

«አሲዱ የማያበላሽው ቢሆን ኖሮ፣ እርስዎ ቀድሞውኑ አሲድ ውስጥ አይከቱትማ!»

* * *

## የዳንስ ምሽት

ጋብሮቮው አንዲት ልጃገረድ ይዞ ፓርቲ ይሄዳል። ይሁን እንጂ ዳንሱ እንደቀለለ ልጂቱ ጋብሮቮውን ገሸሽ ታደርግና ካንድ ጐረምሳ ጋር ዳንኪራዋን ታስነካው ጀመር። ጋብሮቮው ካሁን አሁን ወደኔ ትመለሳለች ብሎ ቢታገስም ጐረምሳው ላይ ተጣብቃ ቀረች። አጅሬ ይኸኔ እየተቆናጠረ ወደ ዳንኪረኞቹ ይገሰግሳል።

ከልጅቱ ጋር ይደንስ የነበረው ጐረምሳ፣ የጋብሮቮው አመጣጥ ስላላማረው ለግብግብ ይዘጋጃል።

ጋብሮቮው ግን ረጋ ብሎ አንዱን የመግቢያ ቲኬት ከኪሱ አወጣና፣ «ዋጋው ሃምሳ ሳንቲም ብቻ ነው ወዳጄ። ገንዘቤን ከመለስክልኝ ሌሊቱን ሙሉ ልታስጨፍራት ትችላለህ» አለው።

* * *

## የማይታጠፍ ቃል

ጋብሮቮው በጣር ይያዝና ከዳነ ፈረሱን ሸጦ በሚያገኘው ገንዘብ በሙሉ ሻማ ሊያበራ ይሳላል። ስለቱ 'ይሰምርናም' አጅሬ ቃሉን ማክበር ሊኖርበት ሆነ። ብዙ ካወጣ ካወረደ




በኋላ ፈረሱ ላይ ዶሮ ጭኖ ገበያ ወጣ።

«ፈረስ በሁለት ሌቭ (ብር) የሚገዛ» ሲልም ይጮህ ጀመር። እጅግ በጣም ርካሽ ዋጋ በመሆኑም ብዙ ገዢዎች ጋብሮቮውን ከበቡት።

ጋብሮቮው ግን «ፈረሱን ከዶሮዋ ነጥዬ አልሸጥም፡ የዶሮዋ ዋጋ 200 ሌቭ ነው» በማለት አስደነገጣቸው።

ይሁንና፣ የማታ ማታ ፈረሱና ዶሮዋ ተሸጠውለት ስለቱን ሊያገባ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ። የፈረሱን ዋጋ የሁለት ሌቭ ሻማ ገዝቶም አበራ።



## ባንድ ድንጋይ...

ጋብሮቮው ራሱን እያዞረው ሰቃይ ቢበረታበት፣ ጓደኛው ደግፎት ወደ ሆስፒታል ይሄዳል:: ዶክተሩ የሕመሙን አይነት ሲጠይቁትም ልቡን፣ ሆዱን፣ ራሱን እንደሚያመው ገለጠላቸው:: ከዚያም አስፈላጊዎቹን መድኃኒቶች እንዲገዛ አዝዘውለት አሰናበቱት::

በሁኔታው የተገረመው ጓደኛው ራሱን ብቻ አሞት ሳለ ለምን ሆዴን፣ ልቤን፣ አሞኛል እንዳለ ቢጠይቀው፣ «ቂል ነህ ልበል? ልጄ ሆዷን፣ ባለቤቴ ደግሞ ልቧን እንደሚያማቸው አታውቅም?»

«እና?»

«እናማ ለልጄና ለሚስቴ ማስመርመሪያ ተጨማሪ ገንዘብ መገበር የምረቅድ ጅል አይደለሁማ!»

* * *

## ድንጋዩ እንዳይጐዳ

መደዳውን የጋብሮቮ ሱቆች ያሉበት አካባቢ ነው:: አንዱ ግድየለሽ ጎረምሳ ገጣጥላውን በእግረኞች መንገድ ላይ መሬት ለመሬት እየጐተተ ይሄዳል:: ይኸኔ ከባለሱቆቹ አንዱ ሮጦ ብሎ፣ «አንተ የማትረባ ጐረምሳ፣ ገንጥላውን ፊትህ አንሳ:: የድንጋዩን ንጣፍ ትጐዳዋለህ!» አለው::

* * *



## ዘመድ ጥየቃ

ጋብሮቮው ዘመዶቹን ሊጠይቅ ሕፃን ልጁን አስከትሎ ገጠር ይሄዳል:: ለላምታ ተለዋውጠው አረፍ እንዳለ ዘመድየው ሕፃኑን፣ «ና ማሙሽ፣ እጅህን ዘርጋና ቆሎ ልስጥህ» ይለዋል::

«ለአባዬ ይስጡት!»

«ቆሎ አትወድም እንዴ፣ ልጄ?»

«እወዳለሁ፣ እማማ:: ላባባ ስጡልኝ ያልኩትም ያባዬ እጅ ከኔው ትልቅ ስለሆነ ቆሎው በርከት ይልልኛል ብዬ ነው::»

* * *

## በጌታ ማመን ቀረ

ጋብሮቫዊቷ አሮጊት ለመቆጠብ ሲሉ የፀሎት መቅረዛቸውን በወይራ ሳይሆን በእህል ዘይት ያበሩ ነበር::

ታዲያ በዚያን አመት ሃይለኛ በረዶ የበቆሎ ማሳቸውን መለመላውን አስቀረው:: መቅረዙን በርካሽ የዘይት አይነት ስላበሩ ቁጣ የወረደባቸው የመሰላቸው አሮጊት መቅረዙ ፊት ተንበርክከው መፀለይ ጀመሩ::

«በይለኛው ባለ ሱቁ ነው፣ አምላኬ:: የወይራ ዘይት አስመስሎ ነው የእህል ዘይት የሸጠልኝ» ሲሉ ተናዘዙ::

ከዚያም መቅረዙን በንፁሕ የወይራ ዘይት ሞልተው

ማብራት ጀመሩ::

ይሁንና በሚቀጥሉት ወራትም፣ በረዶ መጣና የበቆሎውን ማሳ አወደመው:: መበለቲቱ ተበሳጩ:: ለንፁሕ የወይራ ዘይት ያወጡትን ገንዘብ ሲያስቡትማ አበዱ::

«እግዚአብሔር ሆይ! ማናቸውንም ነገር ማየት የምትችል፣ ሁሉን ነገር ማድረግ የማይሳንህ ልትሆን ትችላለህ:: ስለንፁሕ ዘይት ያለህ እውቀት ግን ከማንም ተራ ባለሱቅ አይሻልም» ብለው የእህል ዘይታቸውን ማብራት ቀጠሉ::

* * *

## ያፌሰሰ ሁሉ

የቅዱስ ዮሐንስ እለት ነበር:: ቄሱ እጋብሮቮው መጋዘን ገብተው በባህላቸው መሰረት ጠበል ረጭተው መጨረሳቸው ነበር:: ይሁንና ጋብሮቮው የተለመደውን ስጦታ ማቅረቡን ትቶ መጥረጊያ ሰጣቸውና፣ «አባቴ በዚህ ቤት ባህል መሰረት ውሃ ካርከፈከፉ በኋላ መጥረግ ግዴታ ነው» አላቸው ይባላል::

* * *

## «እንመሳሰላለን?»

«አንተን ባየሁ ቁጥር ያ ቶትዮ ትውስ እንደሚለኝ ታውቃለህ?»



«ኸረ እንዴ,ያውም! እስከዚህ እንመሳሰላለን እንዴ?»

«በመልክስ አትመሳሰሉም:: ግን፣ ቶትዮም እንዳንተው ሃምሳ ሌቭ ተበድሮ አልመለሰልኝም::»

* * *

## ወይ ፍንከች

ሁለት ጋብሮቮ ሾፌሮች ጠባብ ድልድይ ላይ ስለተገናኙ፣ አንደኛው የግድ መኪናውን ወደኋላ አንቀሳቅሶ ሌላውን ማሳለፍ ሊኖርበት ሆነ:: ግን ወደኋላ በመንቀሳቀስ ነዳጅ ማቃጠልን ሁለቱም አልፈቀዱም::

ስለዚህም አንደኛው ሾፌር «አሁን ቁርጡን ሲያውቅ ያሳልፈኝ የለ?» ብሎ ጋዜጣውን ዘርግቶ ማንበብ ጀመረ::

ይኸኔ ሁለተኛው ሾፌር ከመኪናው ወጣና ኮፈኑ ላይ ተንጋሎ ፀሐይ እየሞቀ፡ «የኔ ወንድም፣ ጋዜጣውን አንብበህ ስትጨርስ ታውሰኛለህ?» አለው ይባላል::

* * *


## ብልጥ ለብልጥ

ጋብሮቮው የወይራ ፍሬ ሊገዛ ሱቅ ይሄዳል:: ባለሱቁም ሊያጭበረብረው ሚዛኑ ላይ ትልቅ ምስማር ያስቀምጣል:: ባለሱቁ መዝኖ እንደጨረሰም፣ ጋብሮቮው ኮስተር ብሎ ምስማሩን ከፍሬዎቹ ጋር እየወሰደ፣ «ከፍዬበታለኋ - ልውሰደው እንጂ!» አለው::

## አሸናፊው ማነው?

ከተለያዩ ከተሞች የመጡ ሰዎች ስለየከተማቸው ውበት ሲወያዩ ይቆዩና፣ 'የትኛዋ ከተማ ይበልጥ ቆንጆ ነች' በሚለው ጥያቄ ላይ ግን መጨቃጨቅ ይጀምራሉ። ይሁንና ስምምነት መድረስ ስላልቻሉ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሁሉም የየከተማቸውን ምርጥ የምግብ አይነት ይዘው በመምጣት የከተማቸውን ልዕልና እንዲያስረግጡ ይወሰንና ይለያያሉ።

የሃስኮኛው ተወላጅ የአንድ ሙሉ በግ አሮስቶ፣ የያምቦሎው ሰው ወፍራም ሾርባ፣ የቦርጋሱ ተወላጅ የተጠበሰ ዓሣ፣ የጉርና አር የሆሺስታው ቋሊማ፣ የቶልቡክኑ ትኩስ ዳቦ፣ የፕሎቭዲቡ ፍራፍሬ፣ የሶፍያው የተጠበሰች ዶሮ፣ የካርሎቮው የተቆላ አቾሎኒ፣ የትሮያኑ ብራንዲ፣ የአቤኖቮግራዱ የወይን ጠጅ፣ የራዝግራዱ እርጎ ሲያመጡ፣ ጋብሮቮው ግን ወንድሙን ይዞ መጣ፤ እንዲያባላቸው!



## ዶሮ ማታ

መጠጥ የሚወዱ አንድ የጋብሮቮ አዛውንት፣ ለራት የሚሆናቸውን ባቄላ ቀቅለው ከበሉ በኋላ ትንሽ ይተርፋቸዋል። በማግስቱ ሊበሉት ቢሞክሩ ንፍሮው እጅ እጅ ስላለባቸው ማፍሰስ ሊኖርባቸው ሆነ። ይሁንና ያን ያክል በርካታ ምግብ ማባከኑን ስላልፈቀዱት፣ አንድ ብርጭቆ ብራንዲ ቀድተው «ቫስኮ፣ ይህን ንፍሮ ከበላህ አንድ ብራንዲ እጋብዝሃለሁ። ዶሮ ማታ!» እያሉ፣ ፊታቸውን አኩሳትረው እጅ እጅ የሚለውን ንፍሮ እንደምንም በልተው ጨረሱት።

ከዚያም ብራንዲውን ሊጠጡ ብርጭቆውን ለማንሳት እጃቸውን ከሰደዱ በኋላ ሀሳባቸውን ይቀይሩና እጃቸውን ሰብስበው፣ «ቫስኮ፣ አይበዛብህም? ዛሬ አንድ አገር ንፍሮ ስለበላህ ብራንዲው ለነገ ይደርሕህ» ብለው ብራንዲውን መልሰው ወደ ጠርሙሱ አንቆረቆሩት።

* * *

## ዶሮ ተራ

«ሰማሽ ወይ፣ እንቁላሎችሽ የሰነበቱ ናቸው። ጫጩቶች ሳይኖሩባቸውም አይቀሩ።»

«ታዲያ ምን አሳሰበዎ፣ እሜትዬ! ለጫጩቶቹ እንደሆነ አላስከፍልዎትም።»

* * *

## ጋብሮቮዎች

…የትዳር ጓደኛ ሲፈልጉ ለልብሷ ብዙ ጨርቅ የማትፈጅዋን ቀጭን ልጃገረድ ይመርጣሉ።

…ዋጋ ሲከራከሩ በላብ ይጠመቃሉ።

…ሲጋራ ሲለኩሱም አንዷን ክብሪት እሁለት ሰንጥቀው ነው የሚለኩሱት - ሁለት ጊዜ እንዲጠቀሙባት።

…በክረምት ወራት ቀጥ ያለና ልሙጥ እንጨት ለማገዶ አይገዙም። ይልቁንም ቆልማማውንና ዐይን የበዛበትን እንጨት ይመርጣሉ። ቆልማማው እንጨት ሳይማገድ መፈለጥ ስላለበት እሱን ሲታገሉ በቂ ሙቀትና ያገኛሉና!

* * *

## ዋናው ነገር

ጋብሮቮው መሰላል ላይ ቆሞ ጥገና ሲያካሂድ አዳልጦት ይወድቃል። እንደወደቀም ሕሊናውን ስቶ ጥቂት ይቆይና ይነቃል። በነቃበት ጊዜም ያቀረበው የመጀመሪያ ጥያቄ፣ «ለመሆኑ መሰላሉ ተርፏል?» የሚል ነበር።

* * *

## ለጥምቀት ያልሆነ…

የጋብሮቮው ሚስት፣ «ሾርባው ውስጥ ስንት እንቁላል



ልጨምር?» ስትል ባለቤቷን ትጠይቃለች።

«እእ… ዛሬ በዓል ስለሆነ፣ ግማሽ እንቁላል መጨመር ትችያለሽ» ሲል አባወራው መለሰ።

* * *

## በሚሊዮን የሚቆጠር ኪሣራ

ሁለት ጋብሮቮዎች፣ ባቡር መንገድ ወጥተው ንፋስ ሲቀበሉ አንዱ ባለፀጋ በመርሴዲስ ሲፈስ ያያሉ። ይኸኔ አንደኛው «ያን ሰው ልብ ብለህ ተመልከተው፣ ወዳጄ። ብዙ ሚሊዮን ብር ያከሰረኝ ሰው ነው» አለ።

«አንተ ደግሞ ቀድሞውኑ ምን ገንዘብ ኖሮህ ነው በሚሊዮን የሚቆጠር ብር የምትከስረው?»

«የከሰርኩትማ ልጁን እንዲድርልኝ ብጠይቀው ስለከለከለኝ ነው።»

* * *

## ሥራና ሙዚቃ

ጋብሮቮው ቡና እንዲለቅሙለት ሁለት ልጆች ይቀጥራል። ጀንበር እንደጠለቀችም ሠራተኞቹን ይጠራና ደሞዛቸውን አበላልጦ ይከፍላቸዋል።

ልጅ እግሩ ሠራተኛ በድርጊቱ ተቀይሞ፣ «የኔ ክፍያ ለምን አነሰ?» ሲል ቢጠይቀው፣ «ጓደኛህ ቡናውን ትለቅም በነበረበት ጊዜ ሁሉ ያለማቋረጥ ያፏጭና ይዘፍን ነበር።

አንተ ግን ፀጥ ብለህ ነበር የምትሰራው:: ስለዚህም ነው የሱ ክፍያ የበለጠው» ሲል መለሰለት ይባላል::

* * *

## አዝራር ሽመታ

ባልና ሚስት የተለያዩ ጉዳዮችን አንስተው ሲወያዩ ሚስቲቱ፣ «አሮጌው ኮቴ አንዲት አዝራር እንኳን የለውም:: ይህን ኮት ለብሼ መታየትም እጅግ ያሳፍረኛል» ስትል ተነጫነጨች::

«እሺ ነገ ገበያ ስሄድ እገዛልሻለሁ::»

«ኮት ልትገዛልኝ? ታድዬ!»

«ኮት አልወጣኝም! አዝራር ነው የምገዛው::»

* * *

## ዋናው በር

አንዱ ነጋዴ፣ «ከዚህ ሱቅ ኻያ በመቶ ቅናሽ ታገኛላችሁ!» የሚል ማስታወቂያ እበሩ ላይ ይለጥፋል::

አለፍ ብሎ የሚገኘው ሌላ ባለ ሱቅም ገበያ ለመሻማት፣ «ሰላሳ በመቶ ቅናሽ እናደርጋለን!» የሚል ማስታወቂያ ይለጥፋል::

ይህ «አጉል ፉክክር» እመካከላቸው ያለውን ጋብሮቮ ባለሱቅ ክፉኛ አሳሰበው:: ነገሩን በሚገባ ካሰላሰለ በኋላ



ግን፣ «የቅናሽ ዋጋ ገበያ መግቢያ» የሚል ማስታወቂያ በሩ ላይ ለጠፈ::

* * *

## እፍርድ ቤት

ዳኛ፣ «ባለቤትህን በሸክላ ሳህን በመፈንከትህ በወንጀል ተከሰህ ቀርበሃል:: ባደርግኸው ድርጊት አልተፀፀትክምን?»

«ተፀፅቻለሁ እንጂ! ሳህኑ'ኮ አዲስ ነበር!»

* * *

## ልጅ ወለድኩ ይበል አባት!

«አያቴ፣ ጥርስ አለዎትን?»

«ኧረ የለኝም ልጄ!»

«እንግዲያውስ ኳስ ተጫውቼ እስክመጣ ዳቦዬን ይያዙልኝ::»

* * *

## ረጅም... ያላንድ ቀን አይበልጥ

ጋብሮቮው አደን በተከለከለበት ጫካ ውስጥ ሲያድን ዘበኛ ይይዘዋል:: አጅሬ ግን ዘበኛውን «የዛሬን ብቻ ይማሩኝ:: ሁለተኛም አልረሳም» ሲል ያግባባዋል::

ዘበኛውም ይለቀውና፣ የዚያኑ እለት ማታ ጋብሮቮው

ቤት ይሄዳል:: ከዚያማ ግብዣው ቀልጦ፣ እስከ እኩለ ሌሊት ሲበሉ፣ ሲጠጡ አምሽተው ሲሰነባበቱ ጋብሮቮው፣ «ይሰሙኝ ጌታው! ሌላ ጊዜ ሳድን ከያዙኝ መንግሥት የተመነውን መቀጮ ቢያስከፍሉኝ እመርጣለሁ» አለው::

* * *

## የጋብሮቮዎች መስተንግዶ

ጋብሮቮ የሰነበተ አንድ እንግዳ ሲጋራ ሊያቀጣጥል ክብሪት ሲያወጣ አንዱ መንገደኛ፣ «ክብሪቱን አያባክኑት ጌታው!» ሲል ጮኽበትና የተለኮሰ ሲጋራውን ሰጥቶ አስለኮሰው::

እንግዳውም አመስግኖ ሊሄድ ሲል ጋብሮቮው ፈገግ ብሎ፣ «ጌታው፣ ሊያቀጣጥሏት የነበረችውን ክብሪት ይስጡኝ» አለው ይባላል::

* * *

## አይ አስተዳደግ!

«እማምዬ፣ እባክሽን መቀሱን አቀብዪኝ::»

«እንግዳ ሲኖር ብቻ ነው በመቀስ የምንጠቀመው፣ ልጄ:: አሁን ግን ክሮቹን በጥርስሽ መቁረጥ ትችያለሽ::»

* * *



## ዝርዝር ሒሳቡ ሲተነተን

ጋብሮቮው የሸክላ ድስት ከጐረቤት ይዋስና ይሰበርበታል:: ወዳጅነታቸው በዚህ ምክንያት እንዳይሻክር በማሰብ ሊተካለት ገበያ ይወርድናም ከተሰበረው ድስት ሁለት ጊዜ የሚተልቅና እጅግ ያማረ የሸክላ ድስት ገዝቶ ጐረቤቱ ዘንድ ይሄዳል::

«ሰደናበር ድስትህን በመስበሬ አዝናለሁ፤ ቢሆንም አዲስ ድስት በምትኩ አምጥቼልሃለሁ» ብሎ በፈገግታ አዲሱን ድስት ይሰጠዋል::

ጋብሮቮው ግን ቅር ተሰኝቶ፣ «አዬ! አሮጌው ድስት'ኮ ሊጠጣ የማይችለውን ያህል ቅባት ጠጥቶ በቅቶት ነበር» ሲል መለሰለት::

* * *

## የጋብሮቮ ደም

በጠና የታመመ አንድ የውጭ ዜጋ ጋብሮቮዎች ሆስፒታል ይገባና ደም ይሰጠዋል:: ደም ከተሰጠው በኋላ ስለተሻለውም ደም ለለገሰው ሰው ከፍተኛ ወሮታ ከፈለው::

ሰውየው ለሁለተኛ ጊዜ ደም አስፈለገው:: በዚያን ጊዜ ደም ለለገሰው ባለውለታው የከፈለው ወሮታ ግን ከበፊቱ ያነሰ ሆነ::

ለሦስተኛ ጊዜ ደም ከተለገሰለት በኋላ ግን እስከነጭርሱ ምንም አይነት ወሮታ አልከፈለም፣ ምን ለወጠው? በደም ስሩ ውስጥ የሚዘዋወረው የጋብሮቮ ደም ነበረ!

* * *

## አማራጩ ቢጠፋ

አለቱ ሞቃት ነበር። እንዲያም ሆኖ ግን፣ ዲታው ጋብሮቮ እጅግ በተጨናነቀው ሦስተኛ ማዕረግ ተሳፍረው በባቡር ይጓዛሉ። ታዲያ ሀብታም መሆናቸውን የሚያውቅ አንድ ተሳፋሪ ጮክ ብሎ፣ «ቸርባጂ፣ እንዴት እርስዎ ሦስተኛ ማዕረግ ይሳፈራሉ?» ሲል ቢጠይቃቸው፣ «አራተኛ ማዕረግ ስለሌለ ነው ልጄ!» በማለት መለሱለት።

* * *

## «እኔን አይተህ ተፅናና»

ጋብሮቮው ጉተራ ሊሰራ ይነሳል። ግንበኛ ጠርቶ ዋጋ መደራደር እንደጀመሩም፣ ጉተራው በአስር ቀናት እንደሚጠናቀቅለትና ለግንበኛው በቀን አምስት ሌቭ፣ ለረዳቱ ደግሞ በቀን ሁለት ሌቭ መክፈል እንዳለበት ይረዳል።

«ተጨማሪ ሰው እንኳን አያስፈልግም። እኔው ረዳት እሆንህና ሁለታችን እንሰራዋለን» ሲል፣ ግንበኛውን ያግባባውና ጉተራው ተሰርቶ ያልቃል።



ሂሳቡን ቁጭ ብለው ሲተሳሰቡት ግን አስር ሌቭ ይምታታል።

በዚህን ጊዜ ጋብሮቮው ግንበኛውን ሲያፅናናው፣ «አትበሳጭ ወዳጄ፣፣ አንተ እንኳን አስር ሌቭ ቢጐድልብህም ገንዘብ አግኝተሃል። እኔ ረዳትህ አለሁ አይደለም ስባራ ሳንቲም እንኳ ያላገኘሁ?» አለው ይባላል።

* * *

## ካሣ

ጋብሮቮው መኪናውን እያሽከረከረ ሲሄድ አንዱ እግረኛ ዘሎ መንገዱን ይዘጋበታል። ጋብሮቮው ፍሬኑን ጥርቅም አድርጐ ስለያዘ ጐማው አስፋልቱ ላይ ቢንሸራተትም፣ የመንገደኛው ሕይወት ይተርፋል።

የተደናገጠው እግረኛም፣ ጋብሮቮውን እጅግ በጣም ያመሰግነው ጀመር።

ጋብሮቮው ግን፣ «ምን ያህል ገንዘብ ልትሰጠኝ ትችላለህ?» ሲል ምስጋናውን በጥያቄ አቋረጠው።

«አምስት ሌቭ ብቻ ናት ያለችኝ። ቢሆንም ነፍሴን ስላተረፉልኝ አራት ሌቭ ይውሰዱ።»

«ጐማዬ ሲንሸራተት ስለተበላም ተጨማሪ አንድ ሌቭ ይገባኛል።»

* * *


## «ማን አጨማልቀው አለህ?»

አርቲስቱ ሸራ ጨርቅ ላይ የተሠራ ሥዕሉን ላንድ ጨርቃ ጨርቅ ነጋዴ ሊሸጥ ዋጋ ይነጋገራል::

«ሃምሳ ሌቭ ሽጥልኝ::»

«ምን?! ሃምሳ ሌቭ አልከኝ?! ልሙጡን ጨርቅ እንኳን ካንተ ከራስህ የገዛሁት በአንደ መቶ ሃምሳ ሌቭ ነው::»

«አስታውሳለሁ:: ታዲያ እኔ ስሸጥልህ ጨርቁ ንጹሕ ነበራ!»





## መንገዱ ይኸው ነው

የንግድ ሙያ አልገባህ ያለው አንድ ነጋዴ ከጋብሮቮው ጥቂት ዕውቀት ለመቅሠም ባልንጀራ ያደርገዋል:: ጋብሮቮውም በሐሳቡ ስለተስማማ ዕቃ ሊገዙ ወደ ቦልካን የተራራዎች ሰንሰለት ይሔዳሉ::

ጋብሮቮው መንገዳቸው ላይ ያገኙትን ጠቃሚ ነገር ሁሉ እየገዛ ይሸከም ነበር:: የጥንቸሉን፣ የበጉን፣ የቀበሮውን ቆዳ ሁሉ ገዝቶ ትከሻው ላይ ቆለለ:: አገበሬዎቹ ደጃፍ ድረስ እየሄደ ስለ ላቸውም ቆዳዎቹን የሸጡለት በርካሽ ዋጋ ነበር::

ከሽመታ መልስ ነጋዴዎቹ ስለደከማቸው ዐረፍ እንዳሉ ጋብሮቮው «ስማኝ ወዳጄ!» ይለዋል፣ «ቃል በገባሁልህ መሠረት ማለፊያ ነጋዴ እንዲወጣህ አደርጋለሁ:: አሁን ግን ሦስት መቶ ሌቭ እንድታበድረኝ እፈልጋለሁ:: ካዛንሎስ እንደደረስንም ገንዘብህን እመልስልሃለሁ::»

«ማበደሩንስ አበድርሃለሁ፣ ብቻ አንድ ዐይነት መያዣ እፈልጋለሁ::»

«መያዣማ ይኸውልህ» ብሎ ጋብሮቮው የተሸከመውን እንዳገር ቆዳ ወደ ነጋዴው ትከሻ አሸጋገረው፣ «ዋጋው እንዲህ ቀላል እንዳይመስልህ፣ አራት መቶ ሌቭ ያወጣል» ሲልም አግባባው::

ከዚያም ጋብሮቮው ገንዘቡን ይዞ፣ ነጋዴው ቆዳዎቹን ተሸክሞ ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ካዛንሎክ እንደደረሱ ጋብሮቮው ገንዘቡን አውጥቶ «ገንዘብህ ይኸውልህ ወዳጄ:: አንተም በመያገርነት ያቆየኸውን ቆዳ ስጠኝ» አለው::

ቆዳውን ወስዶም በአንድ ሺ ሌቭ ሸጠና የትርፉን ግማሽ ለጓደኛው ሰጠው:: ገዢዎቹ በራቸው ድረስ ስለመጣላቸው በውድ ዋጋ ገዙት::

ነጋዴ መሆን የሚቻለው በእንዲህ ዐይነት ጥበብ እየተጠቀሙ ነው ወዳጄ:: ሲሔዱ የሚያተርፈውን ሁሉ ይዘው፣ ሲመለሱም እንደዚሁ የሚያተርፈውን ተሸክመው ማትረፍ የተገባ ነው:: ባዶ እጅ መንጠዝጠዝና መንከርፈፉ ግን ዋጋ የለውም» ሲል ምክሩን ለገሠው::

* * *

## ጋቭሮቮዎች

…ቁርስ ሲጋብዙ የቢላዎቻቸውን ጫፎች ያግሉዋቸዋል - ቅቤ (ማርገሪን) በደንብ መዛቅ እንዳያስችሉ::

…ማንኛውንም ነገር ቀለም ሲቀቡ የሚለጥፉት ማስታወቂያ «ቀለም እንዳያበላሽዎ ይጠንቀቁ!» የሚል ሳይሆን «ለቀለሙ እዘኑለት» የሚል ነው::

…በግ አንጠልጥለው አሮስቶ በሚጠብሱበት ዕንጨት ፍቅፋቂ ሾርባ (መረቅ) ያበስሉበታል::



…ለዕንቁላላቸው መሳቢያ ቧንቧ ያስገቡለታልም ይባላል፤ ባንዴ አንድ ዕንቁላል መጨረስ አባካኝነት ነው ብለው ያምናሉ::

* * *

## አንድ ዕንቁላል ሙሉ?

ከዕለታት አንድ ቀን ጋቭሮቮዎች ዘንድ እንግዳ ይመጣና ትልቋ እማማ ለቁርስ ዕንቁላል ቀቅለው ያቀርቡለታል:: በዚህ ያልተለመደ ለጋሥነታቸው የተገረመው ሕፃን ልጅም አፍጦ ይመለከት ጀመር:: አያቱ ግን ሲያጽናኑት «አታስብ ልጄ፣ ወዳጃችን ዓማማ ስላይደለ አንድ ዕንቁላል ሙሉ አይጨርስምና እንደሚያስተርፍልህ እርግጠኛ ሁን» አሉት ይባላል::

* * *

## ለነገ ማለትን አስተማሩት

ጋብሮቮው ወጣት ለናቱ ዕረፍት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ሻማ አብርቶ ሲጸልይላት ከቆየ በኋላ አባትየው ሻማውን ያጠፉታል:: ልጅየውም ተገርሞ ሲመለከታቸው «ቀረውን ደግሞ ነገ እኔ አበራላታለሁ» አሉት ይባላል::

* * *

## ማስታወቂያ

ከጥቂት ዓመታት በፊት 'ናቢ ደኒ' የተባለውን ባለ

ዐሥራ ስድስት ገፅ የመንግሥት ጋዜጣ ጋብሮቮ አካባቢ ለመሸጥ «በሥራ ስድስት ጋዜጦች በአንድ ሌቭ ይግዙ!» የሚል ማራኪ ማስታወቂያ ይወጣ ነበር::

* * *

## ብልጥ ለብልጥ...

«እውን ያ ገንዘብ ተቀባይህ ትልቋን ልጅህን ሊያገባ ነው?»

«አዎን! ሰሞኑን ይጋባሉ::»

«በዚህች ምድር ላይ የማላምነው ፍጡር ቢኖር ይህ ሰው ነው እያልክ ታጫውተኝ አልነበረም?»

«አሁንም አላምነውም:: ጋብቻውን የፈቀድሁትም የሚሠርቀኝ ገንዘብ በተዘዋዋሪ ለልጄ ይደርሳታል ብዬ ነው እኮ::»

* * *

## ራስን ማታለልም ይጠቅማል

ኃይለኛ አጫሽ የሆነ አንድ ጋብሮቮ ሲጋራ ከመለኮሱ በፊት ሲጋራውን ለምን እሁለት እንደሚከፍለው ተጠይቆ ሲያስረዳ «ሁለት ሲጋራ ያጨስኩ ስለሚመስለኝ ብዙ ላለማጤስ በማደርገው ጥረት ስለሚረዳኝ ነው» አለ ይባላል::

* * *



## ኮትህን አውሰኝ

አንድ የሴቭሊየቮ ሰው መርከብ እንደተሳፈረ ጋብሮቮ ጓደኛውን «ኮትህን አውሰኝ ሲል ይጠይቀዋል::

«የራስህ ኮት ምን ሆነብህ?»

«እኔ ዋና ስለማልችል መርከባችን ምናልባት ብትሰምጥ ለኮትህ ስትል እኔን ለማዳን ብርቱ ጥረት ታደርጋለህ ብዬ ነው እንጂ ኮቴስ ምንም አልሆነም::»

* * *

## ገበያ ወዳለበት

የጋብሮቮው ልጅ የልብ ሐኪም ለመሆን የሚያስችለውን ትምህርት በመከታተል ላይ ነበር:: አባቱ ግን በውሳኔው ተበሳጭቶ «አንተ ጅል! የሰው ልጅ አንዲት ልብ ብቻ ስትኖረው ሠላሳ ሁለት ጥርሶች እንዳሉት አታውቅም? በል አሁን ይህን የቂል ትምህርትህን ወደጎን ትተህ የጥርስ ሕክምና ሙያን እንድትከታተል» ሲል መከረው::

* * *

## አርቆ ማስተዋል

ቡልጋሪያዊቷ ዘፋኝ ሀሪስቲና ሞሮፎቫ እጅግ በጣም ወፍራም ነበረች:: ታዲያ ዱሮ ጋብሮቮ ተምራ ኖሮ

ወዳጆቿን ለመጠየቅ ወደዚያው ትሔዳለች።

ይሁንና ያረፈችበት አልቤርጎ ባለቤት ሙፍረቷ ስላሠጋቸው አልጋዋ ሥር ረጅምና ጠንካራ የብረት ማጦን አኖሩ - ያልጋው ሽቦ እንዳይረግብ!

* * *

## ዕንቁላል ተራ

«አምስት የጥቁር ዶሮ እንቁላሎች ይስጡኝ አንቱ» አለች ጋብሮቮዊቷ ዕንቁላል ተራ ሔዳ። ባለ ዕንቁላሏ በነገሩ ተገርማ «እርስዎ የትኞቹ እንደሆኑ የሚያውቁ ከሆነ መርጠው ይውሰዱ» ብትላት አጅሬት ተለቅ ተለቅ ያሉትን ዕንቁላሎች መርጣ ወሰደች።

* * *

## ምርመራ

«አንተ ዘንድ ሊመረመሩ የሚመጡትን ሕመምተኞች ሁሉ ምን እንደሚመገቡ ለምን ትጠይቃቸዋለህ? አመጋገባቸው ስለ ሕመማቸው ይበልጥ እንድታውቅ ይረዳሃል?»

«እንደሱ ሳይሆን ምን ያህል ሊከፍሉኝ እንደሚችሉ ለመገመት ያስችለኛል» አለ ጋብሮቫው ዶክተር።

* * *



## ርካሽ ከሆነ አያጣላም

ጋብሮቮው ለአማቱ የመቃብር ሐውልት ሊያሠራላቸው ይነጋገሩ ባለሙያ ዘንድ ሔዶ «ዋጋው ከፍተኛ ያልሆነ ጥሩ ሐውልት ማግኘት እችላለሁን?» ሲል ይጠይቃል።

«አንድ ቆንጆ ሐውልት አለ። ብቻ የሌላ ሰው ስም ተቀርጾበታል።»

«ግዴለም እወስደዋለሁ። አማቴ እንደሆኑ ማንበብና መጻፍ አይችሉ።»



## ማስታወሻዬ

ብታምኑም ባታምኑም በምሳ ሰዓት ቤቱ እንደምመጣ የሚገልጽ ማስታወሻ ለቶትዮ እቤቱ ትቼለት ነበር፡፡ ታዲያ በቀጠርኩት ሰዓት ቤቱ ብሔድ አጣሁት፡፡

ወረቀትዋ ደርሳዋለች ማለት ነው፡፡

* * *

## «ለኔ ምሳ አታዘጋጂልኝ»

ጋብሮቮው የቤቱን ጣሪያ ራሱ ጠግኖ ወጪውን ለማዳን ይወስናል፡፡ ሆኖም ምንም ዐይነት ዕውቀትም ሆነ ልምድ ስላልነበረው ከጣራው ላይ ተንሸራትቶ ይወድቃል፡፡ እንዳጋጣሚ በማድቤቱ መስኮት አቅጣጫ ቁልቁል ይወድቅ ኖሮ ባለቤቱን «ለኔ ምሳ አታዘጋጂ!» አላት ይባላል፡፡

* * *

## የጋብሮቮ ቅርሶች

በጋብሮቮ የሚገኝ አንድ ቤተ መዘክር ቅርሶችን በጥሩ ዋጋ ለመግዛት ማስታወቂያ ያወጣል፡፡ ይህን የሰማ ጋብሮቮም ጫማዎቹን ተሸክሞ ይቀርብና «ጫማዎቼ ረጅም ዕድሜ ያላቸው ቅርሶች ናቸው» ይላል፤ «ባንደኛው ያለም ጦርነት አባቴ ተጫምቷቸው ነበር፡፡ ከጦርነቱ መልስ እኔ ለሁለት ዓመት ተጠቀምኩባቸው፡፡ ቀጥሎ ባለቤቴ ለቤት ጫማነት ተገለገለችባቸው፡፡ ከዚያ ልጄ 'ጀልባዎች ናቸው' እያለ አንድ ክረምት ሙሉ ተጫወተባቸው፡፡ በመጨረሻም እኔ ራሴ በሁለተኛው ያለም ጦርነት ወቅት ልጫማቸው ተገደድሁ፡፡ በእውነቱ እኒህ ጫማዎቼ በቀላሉ የማይገኙ ቅርሶች ናቸው፡፡»

* * *

## አባብ ለባብ...

«አባቴ ስላበደ ሱቁን እኔ እያካሔድኩት ነኝ፡፡»

«ማለፊያ ነው፡፡ እንግዲያውማ የዕዳ መክፈያ ጊዜዬን ታራዝምልኛለሃ!»

«አልተግባባንም ወዳጄ፡፡ እኔ'ኮ አይደለሁም ያበድኩት፤ አባቴ ነው» ሲል ጋብሮቮው አስረዳው፡፡

* * *

## አልቤርጎ ፍለጋ

ጋብሮቮው መኝታ ፍለጋ ሆቴል ቤት ይሔዳል፡፡

«ላንድ ሌሊት ስንት ነው የምታስከፍሉት?»

«ክፍሉ አንደኛ ፎቅ ከሆነ ዐሥር ብር፣ ሁለተኛ ፎቅ ከሆነ ስምንት ብር፣ ሦስተኛ ፎቅ ከሆነ ስድስት ብር፣ አራተኛ ፎቅ ከሆነ ደሞ አራት ብር ነው የምናስከፍለው፡፡»

ጋብሮቮው ጥቂት አሰብ አድርጎ ከሆቴሉ መውጣት እንደጀመረ በዩ፣ «ምነው? ኪራዩ በዛብዎት?» ሲል ቢጠይቀው፤

«ኪራዩ በዝቶብኝ ሳይሆን ፎቁ አንሶብኝ ነው» አለና ሔደ::

* * *

## የሰው ፍላጎቱ

ጋብሮቮው ቤት ሊገዛ ሲፈላልግ 'ምን ዐይነት ቤት ትፈልጋለህ' ተብሎ ቢጠየቅ፤ እንዲህ ብሎ መለሰ:-

«ሚስቴ ከቤት ሥራዋ ጊዜ ተርፏት ከናቷ ጋር ቁጭ ብላ እንዳታወራ የሚከለክላት ያህል ስፋት ያለውና፤ አማቶቿም አብረውኝ እንዳይኖሩ የሚከለክላቸው ጥበት ያለው ቤት ነው የምፈልገው::»

* * *

## አውቶቡስ ላይ

ጋብሮቮው ልጁን ይዞ አውቶቡስ ይሳፈራል።

«ለዚህ ሕፃን ስንት ነው የምከፍለው?»

«ስድሥቱ ስንት ነው?»

«አምስት::»



«ምንም አይከፍሉም፤ ጌታው::»

«ወንበር ቢይዝስ?»

«ምንም አይከፍልም::»

«እንግዲያው ጭኑ ላይ ባስቀምጠው ስንት ትከፍለኛለህ?»

* * *

## መሃይም መሳይ

ጋብሮቮው ነጋዴ ከመሠረተ ትምህርት ያልተሳቀቀ ሰው የፃፈው የሚመስል ማስታወቂያ ሱቁ በር ላይ ለጥፎ ኖሮ የተለያዩ ሰዎች ማስታወቂያው መሃይም እንደሚያስመስለው ቢነግሩት «ደንበኞቹ በቀላሉ የሚያምኑት መሃይም ያገኙ እንዲመስላቸው ብዬ ነው» አላቸው ይባላል::

* * *

## ሀብታም ለመሆን

አንድ ወጣት ብቻውን የተጠበሰ ሙሉ ዓሣ ሲበላ ያየው ጋብሮቮ «እንዴት ያለኸው አባካኝ ሰው ነህ እባክህ?» ብሎ ከገሰፀው በኋላ የሚከተለውን ምክር ለገሠው::

«ስማኝ ልጄ፤ እኔ አንድ ዓሣ ለአንድ ሙሉ ቀን እንዲበቃኝ አደርጋለሁ:: ጠዋት አሁለት እተክፈለ ዳቦ

መኻል የተጠበሰውን ዓሣ ከትቼ አሻሽቼ ዳቦውን ዘይት ሲነካው ዓሣውን አውጥቼ አሰቀምጬ ዳቦውን ብቻ እበላለሁ። ከዚያም ለምሳዬ ግማሹን ዓሣ እበላና ቀሪውን ለራት አደርገዋለሁ።»

* * *

## «እንኳን ነገርከኝ!»

«ውሻህ ዛሬም አንዷን ዶሮዬን በላብኝ።»

«እንኳን ነገርከኝ። ቀኑን ሙሉ ምንም የሚበላ ነገር አልሰጠውም።»

* * *

## የጉድ መንደር

ጋብሮቮ አካባቢ ያለች ያንድ መንደር ነዋሪዎች አስተማሪ ቀጠሩና በዓመት ከየቤቱ ሁለት፣ ሁለት ባልዲ ብራንዲ (መጠጥ) ሊሠፍሩለት ተዋዋሉ።

ዓመቱ መጨረሻ ላይ መምህሩ ትልቅ በርሜል አዘጋጅቶ ብራንዲውን መሰብሰብ ጀመረ። ሁለት መቶ ቤቶች ስለነበሩም አራት መቶ ባልዲ ደረሰው።

ከዚያም መምህሩ የሰበሰበውን ብራንዲ በሐራጅ እንደሚሸጥ የሚገልጽ ማስታወቂያ አወጣ። ሊገዙት የመጡት ነጋዴዎች ብራንዲውን በቀመሱ ጊዜ ግን እጅግ



ማቁበት፣ ተሟለቁበትም።

ለካስ የአገሬው ሕዝብ 'የኔ ሁለት ባልዲ ውሃ አንድ በርሜል ሙሉ ብራንዲ ውስጥ ብትገባ እጅግም ለውጥ አታመጣም' እያለ ውሃ ሰፍሮለት ኖሯል!

* * *

## ጋብሮቮዎች

...ዋጋ መክራከርን ከማፍቀራቸው የተነሣ ትንሿን ሽርፍራፊ - ማለትም ቡድካ የተባለችውን - የስቶቲንካ ወይም የሳንቲም አንድ ዐሥራ ስድስተኛ ፈጥረዋል።

...ከሱቅ ዕቃ ሲገዙ በዕለቱ በወጣው ጋዜጣ እንዲጠቀለልላቸው ይፈልጋሉ።

...ሊባን ወይም ክር ወድቆ ካገኙ ጣታቸው ዙሪያ በመጠምጠም መጠኗን ይለካሉ። ጣታቸው ላይ አንጓዎ ከዞረች ትጠቅማለች ብለው ስለሚያምኑ ያስቀምጧታል።

...የዶሮዎቻቸውን ዕንቁላል መጣያ ሥፍራ ይበሱና ከረጢት ብጤ ከሥር ይቋጥራሉ። ከዚያም ዶሮዎቹ ዕንቁላል ከጣሉ በኋላ እከረጢቱ ውስጥ ገብቶ ስለሚጠፋባቸው ሌላ ዕንቁላል ለመጣል ጥረት ያደርጋሉ።


* * *

## እፍል ውሃ

«የገላ መታጠቢያ ሳህን ያለውን ክፍል የምታከራዩት ስንት ነው?»

«ሁለት ሌቭ።»

«በል አንድ ሌቭ ይኸውልህ፤ ፈጠን ብለህ ግማሽ ሳህን ውሃ ሙላልኝና ልታጠብ።»



## ቴሌግራም

ጋብሮቮው ለንግድ ክፍለ ሀገር ይሔድና ሽቀጡን እንዳጣራ ለባለቤቱ ቴሌግራም ሊልክ ወደ ፖስታ ቤተ ይሔዳል።

«ሰቃዎቼ በትርፍ ተሸጠዋልና ዓርብ ማታ ጋብሮቮ እገባለሁ። ያንቺው ዲሜተር» ብሎም ፎርሙን ሞላ።



ሆኖም የሚከፍለው ገንዘብ በቃላት ቁጥር ብዛት ስለሆነ ቃላቱ የበዙ ስለመሰለው 'ማሪያ ምንጊዜም አትርፌ እንደምሸጥ ስለምታውቅ ይህን መጥቀስ አያስፈልግም' ይልና ሐረጉን ይሠርዘዋል።

«ዓርብ ማታ ጋብሮቮ እገባለሁ። ያንቺው ዲሜተር» የሚለው መልዕክት ብቻ ይቀራል።

ይሁን እንጂ አሁንም ክፍያው የሚበዛ መስሎ ስለታየው 'ጋብሮቮ መመለሴ የታወቀ ስለሆነ መጥቀስ አያስፈልግም' ብሎ ሠረዘውና «ያንቺው ዲሜተር» የሚለው ቀረ። በመጨረሻም 'የርሷ መሆኔንማ በሚገባ ታውቃለች። ይህንንም ለመንገር ገንዘብ ማውጣት አስፈላጊ አይደለም' ብሎ ፎርሙን ቀዳደደና ከፖስታ ቤቱ ወጥቶ ሔደ።

* * *

## ከፍተኛ መሥዋዕትነት

ከምግብ ሁሉ ርካሽ የሆነውን የባቄላ ሾርባ እየተመገቡ በብዙ ቁጠባ ብዙ ሀብት ያጠራቀሙት አያ ሚንዮ ለከተማይቱ ቤተ መጻሕፍት ዐርባ ሺ ሌቫ በማዋጣታቸው በምረቃው ሥነ ሥርዓት ላይ እንዲገኙ ተጋብዘው በመጨረሻ ስማቸው ለመታሰቢያነት ተጽፎ የሚኖርበትን ሥፍራ ሲያሳዩዋቸው፣

'ሚንዮ እዚህ ለመድረስ ምን ያህል የባቄላ ሾርባ ፈጅተሃል!' ሲሉ በራሳቸው ቀለዱ።

* * *

## ሀ፤ ሁ

አባት ለልጁ አዲስ ጫማ ይገዛለትና ዘመድ ሊጠይቁ ይሔዳሉ፡፡ መንገድ ላይ እንዳሉም አባት «አዲሱን ጫማህን አድርገሃል?» ሲል ይጠይቃል፡፡

«አዎን አባባ!»

«እንግዲያውስ ነቃ ብለህ በረዥሙ መራመድ አትርሳ!»

* * *

## ስንፍና ነዋ!

«ጎረቤቶቻችን ሁልጊዜ ሥጋ የሚበሉት ለምንድነው አብዬ?»

«ተማተም መትከል ስለሚሰንፉ ነዋ፣ ልጄ!»

* * *

## ጺ ጽ!

መኪና በዱቤ የገዛ ጋብሮቮ ዕዳውን ሲከፍል ከተዋዋለበት ገንዘብ ቀንሶ ይከፍላል፡፡ ይህን ያደረገበትን ምክንያት ለሻጮቹ በጽሑፍ ሲያብራራ፣ «የመኪናዋን ክላክስ (ጥሩንባ) የመለስኩት ከጥቂት ልምምድ በኋላ የክላክስ ድምፅ ከአፌ ማውጣት ስለቻልኩ ነው፡፡ ይህ ማስታወሻ እንደደረሳችሁም ቀሪ ሒሳቡን እወራረዳችሁ ከዕዳ ነጻ እንደምታደርጉኝ እተማመናለሁ፡፡ ከምስጋና ጋር የናንተው



ኤም አላታ!» አላቸው፡፡

* * *

## ሊበላ?

ጋብሮቮው ሶፊያ ከተማ ባቡር ጣቢያ ሲደርስ መሽቶ ነበርና ጋሪ ጠርቶ «ከቡናር ሠፈር አድርሰኝ!» ብሎ ይሳፈራል፡፡

ነጂውም «ይኸ ከርፋፋ ጋሪ ሲሳፈር ዋጋ እንኳን አይነጋገርም? ቆይ እንክት አድርጌ እበላው የለ?» እያለ ወደታዘዘበት ሥፍራ ሽመጠጠ፡፡

ከክቡናር አካባቢ ሲቃረቡ ጋብሮቮው «ጉድ ሆንኩ ጃል! እንዴ አቁምልኝ» ሲል ጮኸ፡፡ ከጋሪው ወርዶም ክብሪት ፍለጋ ኪሶቹን እየዳበሰ «በሰው ስሥቅ በኔው ይድረስ? ወቸ ጉድ የወርቅ ጊኒዬ (ዐሥር ሌቭ የሚመነዝር የወርቅ ሳንቲም) ተንከባላ መቀመጫው ሥር ገብታለች፡፡ እንዴ ታገሠኝ ልፈልጋት» አለ፡፡

ይኼኔ ጋሪ ነጂው ፈረሱን ሾጥ አድርጎ ሽመጠጠ፡፡

ጋብሮቮውም ብቻውን እየሣቀ አቅጣጫውን ለውጦ ሔደ፡፡

* * *

## ኩራት እራት

ጋብሮቮው ሱቅ አንድ እንግዳ ተቀምጦ ሳለ ረዳቱ

የወይራ ዘይት ማለቁን ይነግረዋል:: ጋብሮቮው ጮክ ብሎ «ኻያ ሊትር የሚይዘውን ደምበጃን ፈልግና በሱ ሙሉ ገዝተህ ቶሎ ና:: ገንዘቡም ይኸውልህ» ብሎ ካዘዘው በኋላ፣ ጠጋ ብሎ በጆሮው «አምስት ሊትር ብቻ ነው የምትገዛው ልብ አድርግ» ይለዋል::

* * *

## «ሲጋራው ያለቀበት...»

ጋብሮቮው «እዚህ ሰፊ ከተማ ውስጥ የማያውቀኝ ሰው ስለማይኖር በነጻ ሲጋራ ማጤስ መቻል አለብኝ» ብሎ ይነሣል:: ሲጋራ ከመንገደኞቹ ይለምንና ለማስመሰል ሳንቲም አውጥቶ ሊከፍል ይግደረደራል:: ከተሜዎቹ ግን አይቀበሉትም ነበር:: በዚህ ዘዴ ለረጅም ጊዜ ከተጠቀመ በኋላ፣ አንድ ቀን ሶፊያ ባቡር ጣቢያ አካባቢ አንዱ ሲጋራ ይሰጠውና ክስተር ብሎ ሳንቲሙን ይወስድበታል::

«ብልጡ» ጋብሮቮ በዚህ ያልተለመደ ነገር ከመደንገጡ የተነሣ ሊጠይቀው የቻለው አንዲት ጥያቄ ብቻ ነበር - «የየት አገር ሰው ነህ፣ ወዳጄ?»

ያገኘውም መልስ 'የጋብሮቮ' የሚል ነበር::

* * *

## ጋብሮቮዎች

...የሰዓታቸው መዘውሩና ጥርሱ እንዳያልቅባቸው ሰዓታቸውን ማታ ማታ ያቆሙታል::



...የዳንስ ምሽት ሲያዘጋጁ የሌላው መንደር ሙዚቃ ይሰማቸው ዘንድ መርገጫው ጨርቅ የሆነ ጫማ ያረጋሉ::

...ፈረሶቻቸውን ሲመግቡ አረንጓዴ መነጽር ያደርጉላቸዋል:: መነፅር ያጠለቁትም እንስሳት የዕንጨቱ ፍቅፋቂ ድርቆሽ ስለሚመስላቸው የተሰጣቸውን ጥርግ አድርገው ይበላሉ::

* * *

## የገባ ያገለግላል

«የአየሩ ሙቀት ስንት ደርሷል፣ ፍቅርዬ?»

«ዐሥራ አምስት ዲግሪ ሴንቲግሬድ::»

«ውጪውስ?»

«ኻያ ዲግሪ ሴንቲግሬድ::»

«እንግዲያውስ መስኮቱን ክፈቺና አምስቱን ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ወደ ቤት አስገቢው::»

* * *

## እሳት ዐመድ ወለደ

ወጣቱ ጋብሮቮ አዛውንቱ ሚንዮ ዘንድ ሔዶ የንግድ ሥራ ለመጀመር ማቀዱንና የገንዘብ እጥረት እንዳጋጠመው ያዋያቸዋል:: እያ ሚንዮ የወጣቱ ቤተሰቦች ወዳጅ ስለነበሩ የሚፈልገውን ገንዘብ ወዲያውኑ ሰጡት:: ወጣቱም በዚህ እጅግ ተደስቶ ሲጋራ አወጣና በክብሪት ለኩሶ ማጤስ

ጀመረ:: አበዳሪው አዛውንት በወጣቱ ድርጊት ተገርመው እንዴ እሱን ከዚያም ያበደሩትን ጥቅል ብር ተመለከቱና «ልጄ፣ ገንዘቡን ስቆጥር ተሳስቼ ይሆናልና እስኪ መልሼ ልቁጠረው» አሉት:: ጥቅሉን ብር እጃቸው እንዳስገቡም «አባትህ እንኳ እምነት የሚጣልበት ሰው ነበር:: አንተ ግን የጋመ ምድጃ አፍንጫህ ሥር እያለልህ ክብሪት ታቀጣጥላለህ:: ስለዚህ ነጋዴ ልትሆን አትችልም» አሉት ይባላል::

* * *

## የሥራ ክፍፍል

ራቾና ጆርጂ ገንዘብ አዋጥተው አህያ ይገዛሉ:: ቤታቸው እንደደረሱም ራቾ ሆዬ፣ «ውድ ጎረቤቴ የትኛውን ያህያ ግማሽ ነው ንብረትህ ለማድረግ የምትፈልገው?» ሲል ይጠይቀዋል::

«እረ! ምን ይሉታል ይሄን? አህያው እንደሆነ የጋራ ሀብታችን ነው:: ታዲያ መከፋፈል ምን ያስፈልጋል?» ሲል ይመልስለታል::

«አህያው የጋራችን ቢሆንም የትኛው ግማሽ የማናችን እንደሆነ ልናውቅ ይገባል::»

«እንግዲያውስ የፊተኛው ግማሽ የኔ ይሁን» ብሎ ጆርጂ ሳያስብ ይናገራል::

ራቾም «እሺ ይሁንልህ!» ብሎ አህያው ጭራ ሥር



የነበሩትን ዝንቦች ካባረረ በኋላ «ጆርጂ እኔ ለግማሹ አህያዬ አስፈላጊውን እንክብካቤ እያደረግሁ ስለሆነ አንተም የፊተኛውን ግማሽህን መንከባከብ ሊኖርብህ ነው:: እንግዲህ ጥቂት ገብስ አምጣና አህያህን መግበዋ!» አለው ይባላል::

* * *

## እንዱም እንዳይቀር

ገጠሬው ቄስ ሠርግ ቤት ተጠርተው ይሔዳሉ:: ወዲያውኑ ግብዣው ይጀመርና አስተናጋጆቹ ዕድምተኛውን ብራንዲ እያስመረጡ ማስተናበር ይጀምራሉ::

«መምሬ፣ ወይን ጠጅ ልቅዳልዎት ወይስ ብራንዲ?»

«ቢራም በተጨማሪ እፈልጋለሁ ልጄ::»



## ለቢሮክራሲ?

አያ ሚንዮ ለጋብሮቮ በጎ አድራጎት ድርጅት ዐርባ ሺ ሌቫ ስላበረከቱ ይህንኑ ገንዘብ ለማዘዋወር ወደ ባንክ ይሔዳሉ:: ሆኖም የአገልግሎት ዋጋ ሁለት ሌቫ እንዲከፍሉ በተጠየቁ ጊዜ ተበሳጭተው «ሁለት ሌቫ ያለው ሰው መክፈል ይችላል:: እኔ ግን ለቢሮክራሲ የምገብረው ገንዘብ የለኝም» አሉ ይባላል::

* * *

## ባንድ ድንጋይ

«ጋውደር ልቀባም ጌታዬ?»

«ለጋውደሩ ተጨማሪ ገንዘብ ታስከፍለኛለህ ወይስ ከጸጉር ማስተካከያው ዋጋ ጋር የሚታሰብ ነው?»

«ከማስተካከያው ጋር የታሰበ ነው::»

«እንደዚያ ከሆነማ ጋውደሩን በወረቀት ጠቅልለህ ስጠኝ ለባለቤቴ እወስድላታለሁ» አሉ ጋብሮቮው::

* * *

## የመንትያዎች ፎቶ

«ባለቤትህ መንታ መገላገሏን ሰምቼ ደስ ብሎኛል:: ፎቶግራፋቸውን ብታሳየኝ?»

«በደስታ፡ ይኸውልህ::»



«ይኸ ያንደኛው ፎቶ ነው:: ሌላውስ?»

«ስለሚመሳሰሉ ያንዳቸው ፎቶ በቂ ነው::»

* * *

## ወግ - ከአያ ሚኒዮ ቤት

ዝነኛው ጋብሮቮአዊ ነጋዴና ገንዘብ አበዳሪ አያ ሚንዮ ከገጠር ከመጣ እንግዳቸው ጋር ራት ከበሉ በኋላ ዐረፍ ብለው ጨዋታ ሲጀምሩ አያ ሚንዮ መብራቱን ያጠፉታል::

«ጋዙን በከንቱ ለምን እናባክነዋለን ወዳጄ? በጨለማም መደማመጥ እንችል የለም?» ብለው ጨዋታውን እንዲቀጥል ይጋብዙታል::

ከዚያም ማለፊያ ወጎችን ሲኮምኩሙ አምሽተው እንቅልፋቸው ሲመጣ ሚንዮ መብራቱን ሊያበሩ ሲነሡ «አንዴ ይታገሱ አያ ሚንዮ» ሲል እንግዳው ጮኸ::

«ምነው?»

«ሱሪዬ እንዳያልቅብኝ አውልቄው ስለነበረ እስክታጠቅ እንዲታገሡኝ ነው!»

*

## ስጦታዎች

ለጋብሮቮዪቱ ሙሽሪት ሦስት ገንቦላዎች በስጦታ መልክ ከተለያዩ ሰዎች ይመጡለታል:: የጫጉላ ጊዜዋ

እንዳበቃም ከሦስቱ አንዱን ጉርንጥላ በሌላ ዕቃ ለመለወጥ ወደተገዛበት ሱቅ ይዛ ትሔዳለች:: ባለሱቁ ግን ጉርንጥላውን አገላብጦ ከተመለከተ በኋላ «አዝናለሁ እሜቴ! ይህ ጉርንጥላ የተገዛው ከዚህ ሱቅ አይደለም» ይላታል::

«ጉርንጥላው መያዣ ላይ የተንጠለጠለው ጽሑፍ የሚጠቅሰው የዚህን መደብር ስም አይደለም እንዴ?»

«የተጠቀሰው ስም በርግጥ የኛ ነው:: ሆኖም እዚህ ሱቅ ጉርንጥላ እንጠግናለን እንጂ አንሸጥም::»

ሙሽሪት በነገሩ ተበሳጭታ ወደቤቷ እንደተመለሰችም ሌሎች ጉርንጥላዎች ላይ የተንጠለጠሉትን ጽሑፎች ብትመለከት ሁሉም አንድ ዐይነት ሆኑባት - የተጠገኑ ጉርንጥላዎች ብቻ!

* * *

## መልካም አጋጣሚ

«ፔንቼቭን ብዙ ምግብ እንዳይበላ ሐኪሙ እንዳዘዙት ሰምተሃል?»

«አረ አልሰማሁም:: እንግዲያውማ ነጋ ማታ ራት እንጋብዘዋለን::»

* * *



## እንወራረድ፤ አህያ እንረድ

ሁለት ጋብሮቮዎች 'ለቤተክርስቲያን ዝቅተኛ ምጽዋት የምትሰጥ አንተ ነህ፣ አንተ ነህ' በመባባል ሲወነጃጀሉ ቆይተው ወደ ቤተክርስቲያኑ ጎራ ይላሉ::

ቅዳሴው እንዳበቃም አገልጋዩ የምጽዋት ሙዳዩን እያዞረ ወደነሱ ሲቀርብ አንደኛው ጋብሮቮ አንዲት ስቶቲንካ ሰጥቶ ጓደኛውን በንቀት ሲመለከተው፣ አጅሬ በትሕትና አማትቦ «ምጽዋቱ የሁለታችንም ነው» በማለት አገልጋዩን አሰናበተው::

* * *

## የቸገረው እርጉዝ ያገባል

«ሠራተኛዬ ስኳር እየሰረቀች አስቸግራኛለች:: ያንቺስ ሠራተኛ እንዴት ነች?»

«የኔዋ መስረቅ ብትፈልግም አትችልም::»

«እንዴት አባክሽ?»

«የስኳር ዕቃዬ ውስጥ ሁልጊዜ ዝንብ ስለማስቀምጥ ሠራተኛዬ ክዳኑን ከከፈተችው ዝንቡ ይበራል:: ዝንቡን እቦታው ካላገኘሁት ደግሞ እጥጋቢ ምክንያት ስለምሻ ሠራተኛዬ ደፍራ አትሰርቅም::»

* * *

## ዕቃው

አዛውንቱ ጆርጂ ከጋብሮቮ ወደ ሶፊያ እንደመጡ አንድ ዕቃ ጠቅልለው አውቶቡስ ይሳፈራሉ:: ቲኬት ቆራጩም «ሦስት ሌቭ ለዕቃዎ ይከፈሉ» ይላቸዋል::

ይኼኔ አጅሬ ጆንያቸውን እየፈቱ:: «ፔንቾ ና ውጣ አባክህ፤ እንዲያውም ዕቃ ስትሆን ነው ክፍያው የሚበዛው» አሉት ይባላል::





## ያለፈበት አራዳ

የኤለና ተወላጅ የሆነ ሰው ጉድጓድ በነጻ ማስቆፈር ይፈልጋል:: አንድ ጂፕሲ ጠርቶም «ኮንስታንቲኖፕል ያለው ሆጃ (ሼክ) በጻፈልኝ ደብዳቤ መሠረት እዚህ ውስጥ የተቀበረ ከፍተኛ ሀብት ስላለ ቦታውን ላሳይህና ቆፍር:: የምታገኘውን ወርቅም እኩል እንካፈላለን» ይለዋል::

«ጌታው ኮንስታንቲኖፕል የሚኖረው ሆጃ የሚናገርን ማመን ያዳግተኛል:: ምክንያቱም ከዚህ በፊት ልክ እንደርስዎ ላንዱ ጋብሮቮ ደብዳቤ ጽፎላቸው የውሃ ጉድጓድ ያክል ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ቆፍሬ ከውሃ በስተቀር ምንም ሳናገኝ ቀርተናል» ሲል መለሰለት::

* * *

## ንብረት ማውደም ያስቀጣል

ጋብሮቮው ታንቆ ሊሞት ይወስናል:: ይሁን እንጂ ገመዱን ቋጥሮ አንገቱ ውስጥ እንዳስገባ አሽከሩ ይደርስና ገመዱን ቆርጦ ያድነዋል::

ወሩ መጨረሻ ላይ ጌትየው አንድ ሌቭ ከአሽከርየው ደሞዝ ላይ ይቆርጣል:: አሽከርየው ምክንያቱን ቢጠይቀው የሒሳቡ ተቆራጭ የዚያ የቆረጠው ገመድ ዋጋ መሆኑን ገለጸለት::

* * *

## ጋብሮቮዎች

...ቤታቸውን የሚሠሩት ጠባብ መሠረት ላይ ሲሆን ቤቶቹ ወደላይ ከፍ እያሉ ሲሔዱ ግን እየሰፉ ይሔዳሉ:: መሠረቱን ጠባብ የሚያደርጉትም የመሬት ግብር እንዳይበዛባቸው ነው::

...ለሚያፈቅሩአቸውና ለሚያከብሩአቸው እንግዶች ርግቦችን በስጦታ መልክ ያበረክታሉም ይባላል:: እንግዶቹ ቤታቸው ደርሰው ርግቦቹን ሲለቁዋቸው ተመልሰው ወደቀድሞ መኖሪያቸው ይበራሉ::

...ለንግድ ሶፊያ ሲሔዱ ፍልውሃ ከሆነው ምንጭ ሙቅ ውሃ በመጠጣት የሻይ ወጪያቸውን ይቆጥባሉ::

* * *

## ከዜሮ ተነሥቶ

ከጋብሮቮ የመጡ ወዳጆች ቡና እየጠጡ ሲጫወቱ፣ ከመካከላቸው ሀብታም የሆነውን ከምንም ተነሥቶ እንዴት እዚህ ሊደርስ እንደቻለ ይጠይቁታል::

«ለአብነት ያህል፣ ሚስቶቻችሁ ሾርባ ሲሠሩ ምን ያክል ሩዝ እንደሚጨምሩ ታውቃላችሁ?» ሲል መልሶ



እነርሱኑ ይጠይቃቸዋል::

«የሚያስፈልገውን ያህል ነዋ!»

«ባለቤቴም የምትጨምረው ልክ የሚያስፈልገውን ያህል ነው:: ሩዙን ወደ ድስቱ ከመጨመሯ በፊት ግን፣ አንድ ዐሥራ ሁለት ፍሬ ያህል ትቀንስለታለች:: ዛሬ አንድ ደርዘን ፍሬ፤ ነገ አንድ ደርዘን ፍሬ...አስቡታ እንግዲህ»

* * *

## ኩንትራታችን አይፈቅድም

ጋብሮቮው እባንክ ቤት በር ላይ በቆሎ እየጠበሰ መሸጥ ይጀምራል:: ባለሙያ ኖሮ የሚያዘጋጀው በቆሎ ይወደድለትና ባጭር ጊዜ ውስጥ ይከበራል:: ታዲያ ይህን ያስተዋለ አንድ ያገሩ ሰው ገንዘብ እንዲያበድረው አስተዛዝኖ ቢለምነው «አዬ ወዳጄ፤ ይህን በቆሎ መጥበሻ እዚህ ሳቆም ከባንክ ቤቱ ጋር ምንም ዓይነት ውድድር ላለማድረግ ቃል ገብቻለሁ:: በውላችን መሠረት ባንኩ በቆሎ ጠብሶ መሸጥ አይችልም፤ እኔም ገንዘብ ማበደር አልችልም» ብሎ ሸኘው::

* * *

# ቁጭት

ጋብሮቮው ልጅ፣ መንገድ ዳር እየተንሰቀሰቀ ያለቅሳል::

«ለምን ታለቅሳለህ፣ ማሙሽ?»

«እናቴ የሰጠችኝ አንድ ሌቭ ጠፋብኝ::»

«በል ተወው አታልቅስ፤ እንካ አንድ ሌቭ::»

ልጁ ታዲያ ገንዘቡን ከተቀበለም በኋላ ልቅሶውን ቀጠለ::

«አሁን ደግሞ ምን ያስለቅስሃል አንተ?»

«የመጀመሪያው ሌቭ ባይጠፋብኝ ኖሮ አሁን ሁለት ሌቭ ይኖረኝ ነበር::»





# ምንም ብታንስ ገንዘብ ናት

ዝርዝር በማጣቱ ለደንበኛው የአንድ ስቶቲንኪ (ማንቲም ያክል እንደማለት ነው) መልስ መስጠት የቸገረው ባለሱቅ፣ «ዝርዝር ስለሌለኝ በምትኩ ምን ልስጥዎት?» ሲል ይጠይቃል::

«አትጨነቅ ወዳጄ፤ አንድ ብራንዲ ትግዛልኝና ዕዳህን እንዳወራረድህ እቆጥርልሃለሁ» በማለት ጋብሮቮው መለሰ::

* * *

# ባልና ሚስት ካንድ ወንዝ ይቀዳሉ

አንድ የጋብሮቮ ጉብል የከንፈር ወዳጁን ቤተሰቦቿ ከቤት እንደወጡ ቤቷ እንደሚመጣ ይነግራታል:: ሆኖም ካልታሰበ እክል ራሳቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ልጅቱ ቤቱን በሚገባ እንድትፈትሽና በመጨረሻም መስኮቱ ሥር ሳንቲም ስትጥል እሱ እንዲገባ ይስማማሉ::

ቀጠሮው ደርሶ ልጅቱ ሳንቲሙን ጥላ የሚንቃጨል ድምጽ ከተሰማ በኋላ ጐረምሳው ሳይገባ ብዙ ይቆያል:: ልጅቱ በሩን ከፍታ ስትወጣ አጅሬን መስኮቱ ሥር ተንበርክኮ ዕቃ ሲፈልግ ታየዋለች::

«ከመግባቴ በፊት ሳንቲሟን ማግኘት አለብኝ ብዬኮ ነው የምንደፋደፈው::»

«በከንቱ አትድከም። እኔ ቀድሞውኑ በክር አስሬያት ስለነበር ከተንቃጨለች በኋላ በክሩ ስቤ ቦርሳዬ ከትቻታለሁ» አለችዋ፣ በፈገግታ።

* * *

## ልቁ አንበሳ

ባለሱቁ አንበሳ ያለበት ከሩቅ የሚታይ የንግድ ምልክት እንዲሠራለት ካንዱ ጋብሮቮ ሠዓሊ ጋር ይዋዋላል። «የታሰረ አንበሳ እንዲሣልሎት ነው የሚፈልጉት ወይንስ ልቁን? የታሰረውን ከፈለጉ ሁለት መቶ ሌቨ ይከፍላሉ፤





ልቁን የሚሹ ከሆነ ግን ባንድ መቶ ሌቭ እሠራልዎታለሁ።»

«እንግዲያው ልቁን ሣልልኝ።»

«ሠዓሊው ወዲያውኑ ሥራውን አጠናቅቆ አስረከበ። ባለ ሱቁም ከበሩ ላይ ሰቀለው። ይሁንና የዚያን ዕለት ኃይለኛ ዶፍ ጥሎ ስላደረ ባለሱቁ ሥራ ሲገባ አንበሳውን ከሥፍራው ያጣዋል። እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ አርቲስቱ ዘንድ ይሄድና አንበሳውን ውሰድ ቢለው፣ «ጌታው፤ እንድሥልልዎት የጠየቁኝ ያልታሰረ አንበሳ አልነበረም? ልቅ አንበሳ ቢጠፋ እንዴት ይደንቅዎታል?» በማለት ጋብሮቮው በርጋታ ይመልስለታል። ያልታሰሩ አንበሶችን የሚሥለው በውሃ ቀለም፣ የታሰሩትን ግን የሚሠራው በዘይት ቀለም ነበራ!

* * *

## ቂልዎን ይፈልጉ ዶክተር!

ጋብሮቮው ሕመሙ ሲጠናበት፣ 'ለመጀመሪያ ምርመራ ሁለት ሌቭ ነው የሚያስከፍሉት። ለሁለተኛ ጊዜ ሲኬድ ግን አንድ ሌቭ ነው የሚያስከፍሉት። እንግዲያው ለሁለተኛ ጊዜ የመጣሁ ባስመስል በአንድ ሌቭ ይመረምሩኛል' ብሎ ሐኪም ዘንድ ይሄድና፣ «ዶክተር ያለፈው ጊዜ ያዘዙልኝ መድኃኒት ምንም አላሻለኝም» ይላቸዋል።

አዝማሚያው ያላማራቸው ዶክተርም በሽተኛውን በጥንቃቄ መርምረው መድኃኒት ያዙለታል።

ጋብሮቮው ይኸኔ «ዶክተር ለዚህ ትእዛዝዎ ያለፈው ጊዜ ስለከፈልኩዎት አሁን ምንም መክፈል አይኖርብኝም» በሎአቸው ወጣ።

* * *

## የጥርስ ሐኪም ዘንድ

ጋብሮቮው የጥርስ ሕመሙ ቢበረታበት ሐኪም ዘንድ ሄዶ «ለምርመራ ስንት ያስከፍሉኛል፣ ዶክተር?» ሲል ይጠይቃል።

ሐኪሙም «የተበላሸውን ጥርስ ለመንቀል ሁለት ሌቭ፣ ጊዜው ምሽት ስለሆነ ለመብራት ደግሞ ተጨማሪ አንድ ሌቭ፤ በድምሩ ሦስት ሌቭ ትከፍላለህ» ይሉታል።

«ማለፊያ ነው፤ ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ እመጣለሁ።»

* * *

## ለናሙና

ጋብሮቮው ጉብል ለእጮኛው ፎቶግራፉን ሊልክላት ፖስታ ቤት ይሄዳል። እና ደብዳቤውን ለመላኪያ ብዙ ገንዘብ ላለማውጣት ሲል ፖስታው ላይ «ለናሙና የተላከ፣ ትርፍ የማይገኝበት ዕቃ!» ብሎ በትልቁ ፃፈበት።

* * *



## ቀዳዳዎቹ የታሉ?

ከጋብሮቮ መንደር የመጣ አንድ ገበሬ ሶፍያን (የቡልጋሪያ ርዕሰ ከተማ) እየተዘዋወረ ሲጎበኝ ውብና ማራኪ የሆነውን 'ፓናማ' የተባለውን ባርኔጣ ቢያይ የሰሌን ባርኔጣ ያገኘ መስሎት ሊገዛ እሱቅ ይገባል።



«የዚህ ባርኔጣ ዋጋው ስንት ነው?»

«ኻያ ሌቭ!»

ገጠሬ በመሆኑ ባለሱቁ የሚያሾፍበት የመሰለው ጋብሮቮ «ታዲያ ቀዳዳዎቹ የታሉ?» ሲል ይጠይቀዋል::

«ምን የሚሆኑ ቀዳዳዎች?»

«ለሰሌን ባርኔጣ ይህን ያክል ገንዘብ ለሚያወጣው አህያ ሰው ጆሮዎች ማሾለኪያ የሚሆኑት!»

* * *

## ከኦፕራሲዮን በፊት

በሽተኛው ቦርሳውን አውጥቶ ብሩን መቁጠር ሲጀምር ዶክተሩ አይተው፣ «አታስብ ወዳጄ፣ ኦፕራሲዮንህ ከተጠናቀቀልህ በኋላ ትከፍላለህ» አሉት::

ሕመምተኛው ጋብሮቮ ግን «ምን ያክል ገንዘብ እንዳለኝ በትክክል ለማወቅ ፈልጌ ነው፣ ዶክተር» በማለት ያልጠበቁትን መልስ ሰጣቸው::

* * *

## ማለፊያ አሻሻጭ

«ይኸ ጨርቅ በእርግጥ አዲስ ነው?»

«አዎ እመቤቴ:: ገና ትላንትና ነው ከፋብሪካ የመጣው::»

«እሱስ በጄ፤ ቀለሙ ቶሎ አይለቅ ይሆን?»



«በኔ ይሁንብዎ እሜትዬ፤ ሱቃችን መስኮት ላይ ከተሰቀለ እንኳን ወሩን ይደፍናል:: በቀን በቀን ፀሐይ ይመታዋል:: እንደዚያም ሆኖ እንደሚያዩት ገና አዲስ ነው::»

* * *

## በነፃ ሲገኝ

ጋብሮቮ የንስሃ አባታቸውን ሊጠይቁ የሄዱ ጓደኛሞች ስለ መብራት ጉዳይ ውይይት ይከፍታሉ::

«አባታችን ለምን በሻማ ይገለገላሉ? የኩሬንቲ ዋጋ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን ያውቁ የለም?»

«አውቃለሁ ልጆቼ፤ ሻማዎቹን ግን የማገኛቸው በነፃ ነው::»

* * *

## «እኔ በለፋሁ ሌላው ሊበላ?!»

ጋብሮቮው ሻንጣውን ትከሻው ላይ እንዳደረገ አውቶቡስ ይሳፈራል:: ትኬት ቆራጩም ለእቃው ጭምር እንዲከፍል ይጠይቀዋል:: ጋብሮቮው በዚህ ክፉኛ ተበሳጭቶ «እኔው ራሴ ለምሸከመው እቃ እንዴት ክፈል እባላለሁ? አይደረግም!» ብሎ ድርቅ አለ::

* * *

## አነሰኝ ሲሉ...

አስፈላጊው ሕክምና ከተደረገለት በኋላ በጣም ጥቂት ገንዘብ በከፈላቸው በሽተኛ የተናደዱት ዶክተር «ይህ ገንዘብ ለኔ ነው ወይስ ለተላላኪዬ?» በማለት የምፀት ጥያቄ ቢያቀርቡለት፣ ጋብሮቮው ፈገግ ብሎ «ለሁለታችሁም ነው፣ ዶክተር» ሲል መለሰላቸው።

* * *

## መሬት ቀድማ አትብላን...

ጋብሮቮው እንግዶቹን ድንች ጋብዞ «እረ አትግደርደሩ፣ ብሉ። ጓሮ ያፈራው ነው'ኮ። የተሸመተ አይምሰላችሁ!» እያለ ያግባባቸዋል።

«ለገበያ የሚሆን ድንች ማቅረብ የሚያስችልህ እርሻ አለህ እንዴ?»

«ሰፊ እርሻ እንኳን የለኝም። ሆኖም ላሮጊቷ ባለቤቴና ለራሴም ማረፊያ የሚሆን የመቃብር ቦታ ገዝቻለሁ። ታዲያ እስክንቀበርበት ድረስ ብንጠቀምበት ብዬ ድንች እየተከልኩበት ነው።»

* * *

## ፍላጐቷን ለማርካት

«ለባለቤቴ ምን አይነት ስጦታ መስጠት እንደሚገባኝ እያሰላሰልኩ ነው እባክህ።»



«እኔ ብዙውን ጊዜ የማበረክትላት ስጦታ ወደፊት ራሴ ልጠቀምበት የምችለውን አይነት ነው።»

«እኔ እንኳን ልሰጣት የምፈልገው ገፀ በረከት ለርሷ ብቻ የሚሆናትን አይነት ነው።»

«እንግዲያውስ አንድ ሳሙና ግዛላት።»

* * *

## ሆድ ሲያውቅ...

ሁለት የጋብሮቮ ተማሪዎች ባርኔጣ ገዝተው ከሱቅ ሲወጡ ኃይለኛ ዝናብ መጣል ይጀምራል። በረንዳ ላይ ቆመው ምን ማድረግ እንደሚሻላቸው ሲወያዩም አንድ ሀሳብ ይመጣላቸዋል፣ ባርኔጣ መለዋወጥ። ባዲሱ ሀሳብ መሰረት አንዱ ጋብሮቮ የሌላውን ባርኔጣ ያደርግና በመበስበስ ላይ ያለው ባርኔጣ የሱ አለመሆኑን እያሰበ ተፅናንቶ በሰላም ይጓዛል።

* * *

## የጋብሮቮ መስተንግዶ

እንግዳው ሃይለኛ ዝናብ ይይዛቸውና አንዲት ጋብሮቮ ባልቴት ዘንድ ይጠለላሉ። ዝናቡ እንዳባራም አሮጊቷ ንፋስ ያረገፈውን ፍሬ በመሰብሰብ ለእንግዳው ያቀርቡላቸዋል። ግብዣቸውን ሲያሳምሩም «ይብሉ እንጂ ጌታው። ረጅም መንገድ የተጓዙ ይመስላሉ። እባክዎን ይብሉ፣ እኔ

እንደሆንኩ በዚህ አመት የረገፈ ፍሬ የምቀልበው አሣማ የለኝም» አሉዋቸው::

* * *

## ጋብሮቮዎች

...ምሳ ከበሉ በኋላ አጥንቱን ለጥርስ ማስቅስቂያ ያጠራቅሙታል ይባላል::

...ለቤታቸው ጢስ መውጪያ መጥረጊያ እንዳይገዙ ድመቶቻቸውን ጢስ መውጫው ውስጥ ይወረውራሉ ይባላል::

...ቤት ሲከራዩ በተቻለ መጠን የመንገድ መብራት እመስኮታቸው አጠገብ መኖሩን አረጋግጠው ነው::

...ማታ ማታ የዶሮ ቤታቸው ላይ መብራት ያበራሉ - ዶሮዎቻቸው ቀን መስሏቸው እንቁላል እንዲጥሉላቸው::


...ለንግድ ወደ ውጭ አገር ሲሄዱ ሾርባ የሚያዘጋጁት በህብረት አንድ ማሰሮ ውስጥ ነው:: ሆኖም እያንዳንዳቸው የራሱ ቁራጭ ሥጋ ላይ ልዩ ምልክት ያደርጋል - ያንዱን ሥጋ ሌላው እንዳይበላበት::

* * *



## ለተሻለ ውጤት ልዩ ማነቃቂያ

የጋብሮቮ የእግር ኳስ አሰልጣኞች ግብ ጠባቂዎቻቸውን ሲያለማምዱ፣ «ኳሷ ጐል ገብታ መረቡ የተበጠሰ እንደሆነ የመረቡ ዋጋ ከደመወዝህ ይቆረጣል» ይሏቸዋል ይባላል::



## ወቅቱን ጠብቅ ልጄ!

«አብዬ አንድ ሌቭ ስጠኝና ለባለ ቴሌስኮፑ ከፍዬ ጨረቃን ልያት::»

«አትቸኩል ልጄ:: ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ሙሉ ጨረቃ ስለምትሆን ያኔ በዚሁ ዋጋ ታያታለህ::»

* * *

## ዘይቱን ማዳን - በዘዴ

ባልቴቷ ጋብሮቮ በየቀኑ መቅረዛቸውን እያበሩ ለብዙ ሰዓታት ፀሎት ያደርሱ ነበር:: ይሁንና ልጃቸው በሚያባክኑት ዘይት ብዛት አልተደሰተም:: ስለዚህ አንድ ምሽት ቀም ሳጥኑ ውስጥ ተደብቆ ይቆይና ባልቴቷ ፀሎት ሲጀምሩ ድምፁን አለስልሶ «ጋና ይበቃሻል:: ፀሎትሽ እምሳከሽ ዘንድ ደርሷል» ይላቸዋል::

* * *

## ፋክክር

እንግዲህ የስኮትላንድ ሰዎችም እንደ ጋብሮቮዎቹ እጅ በጣም ቆጣቢዎች ናቸው ይባላል::

ጋብሮቮዎች የሰአቶቻቸው ጥርሶች ቶሎ ተበልተው እንዳያልቁባቸው ማታ ማታ ሰአቶቻቸውን ያቆማሉ የሚል ወሬ የሰማ የአበርዲን (እስኮትላንድ) ተወላጅ «ለመሆኑ ምሽት ላይ ሰዓት ስንት መሆኑን በምን ሊያቁ ይችላሉ?» ሲል አሰበ::

ጥቂት ካሰበ በኋላ ግን እስኮትላንዶች ከጋብሮቮዎች ያላነሱ ብልሆች መሆናቸውን ለማሳወቅ «እኛ አገር ደሞ ከዚህም የባሰ ጉድ አለ!» ብሎ የሚከተለውን አጫወታቸው::

ትራስጌው ዋሽንት እያስቀመጠ የሚተኛ አንድ ጐረቤት አለኝ:: ስንት ሰዓት እንደሆነ ማወቅ በሚፈልግበት ጊዜ ታዲያ መስኮቱን ይከፍትና ዋሽንቱን መጫወት



ይጀምራል:: ይህን ጊዜ ከጐረቤቶቹ አንቅልፍ እምቢ ያለው አንዱ «ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ተኩል ላይ ዋሽንት የሚነፋው ምን አይነቱ ጅል ነው እባካችሁ?!» ብሎ መጮሁ አይቀርም::

* * *

## አያሻም

የጋብሮቮውን መጠጥ ቤት የሚያዘወትር አንድ መሸተኛ ነበር:: ታዲያ አንድ ቀን የሚጠጣው ነገር ቀጠንጠን ስላለበት ጎዶት እየተናነቀው «ስማ ሰውዬ፣ ወይን ጠጁ ውስጥ ውሃ ጨምረህበታል!» ቢለው፣

«ለምን አጉል አተካራ ታስነሳለህ ወዳጄ! ለውሃው እንደሆነ አላስከፍልህም» ብሎ መለሰለት::

* * *

## «የጋለ አቀባበል ተደረገላቸው!»

አንዱ ጋብሮቮ ቤት የተገኘ የደብዳቤ ብጫቂ እንደሚከተለው ይነበባል::

«ውድ አጎቴ፣

ባቡር ጣቢያ ተገኝቼ ልቀበልህ ባለመቻሌ በጣም ይቅርታ እጠይቃለሁ:: በኔ ምትክ ባለቤቴ እስፍራው ተገኝታ አቀባበል ታደርግልሃለች:: ግን ከዚህ ቀደም አይታህ ስለማታውቅ፣ ከሌሎች መንገደኞች ለይታ ታውቅህ ዘንድ

በግራ እጅህ ግልገል ዓሣማ፣ ካልሆነልህም ቢያንስ አውራ ዶሮ አንጠልጥለህ እንድትመጣ ይሁን:: ያንተው...»

* * *

## ቃልኪዳን

ከብዙ ዓመታት በፊት የቡርዥዋው (የከበርቴው) ፓርቲ ተመራጭ ለጋብሮቮ ሕዝብ ባደረገው ንግግር «ፓርቲያችን ስልጣን ከያዘ ጨው ላይ የተጣለውን ቀረጥ ስለሚያነሳ ምግባችሁ ውስጥ ያሻችሁን ያክል ጨው መጨመር ትችላላችሁ» ሲል ቃል ገብቶላቸው ነበር::

* * *

## ማለፊያ ምክር

«ጐረቤታችን አንድ መቶ ሌቭ እንዳበድረው ጠይቆኛል:: ምን ይመስልሃል?»

«እረ አበድረው ወዳጄ:: ካበደርከው ለኔም ውለታ እንደዋልክልኝ ነው የምቆጥረው» አለ አጅሬ - ጐረቤቱ ገንዘብ ካላገኘ ዞሮ እርሱኑ ብድር እንደሚጠይቀው በመስጋት::

* * *

## ዲፕሎማቶች

የአበርዲን (እስኮትላንድ) ተወላጅ የሆነ ሰው በቅርብ ጊዜ ከተዋወቀው ጋብሮቮ ጋር ወደ ሆቴል ቤት ይሄዳል::



ለሁለት አንድ ዓሣ ያዙና ይመጣላቸዋል:: ዓሣው ከወደጭራው ቀጠን ማለቱን ሁለቱም ያስተውላሉ:: ይሁን እንጂ ስስታም ላለመምሰልና ጨዋነታቸውን ለማሳየት ሁለቱም ዓሣውን አይን አይኑን ሲያዩት ቀዘቀዘ:: በመጨረሻ ግን የዓሣው ጭራ ወደሱ በኩል የተደቀነበት የአበርዲን ሰው ወግ ጀመረ::

«ወዳጄ! ዲፕሎማት ምን አይነት ሰው እንደሆነ ታውቃለህ?»

«እረ አላውቅም አያ!» አለ ጋብሮቮው::

የአበርዲኑ ሰው ሳህኑን ዘወር አድርጎ ወፍራሙን የዓሣ ክፍል ወደ ራሱ በኩል ካደረገ በኋላ «ዲፕሎማት ልክ እኔ አሁን ሳህኑን እንዳሽከረከርኩት ዓለምን የሚያሽከረክር ሰው ነው::»

«ደግ ጨዋታ ነው:: ለመሆኑ አንተስ ዲፕሎማት ነህ?»

«አይደለሁም::»

«ታዲያማ ዓለምን ቀድሞ እንደነበረችው ለምን አትተዋትም?» ብሎ ጋብሮቮው ሳህኑን ቀድሞ ወደነበረበት መለሰው::

* * *

## «ተወው»

ግብር ለብሳቢው ቡና ቤት ሲገባ አንዱ ድሃ ጋብሮቮ አየውና አስተናጋጁን ጠርቶ «አንድ ቡና ለጌታዬ - ለግብር

ሰብሳቢው - አቅርብላቸው» ሲል አዘዘው::

ሆኖም «ግብር ሰብሳቢነቱ ከቀረ'ኮ ዘመን አልፎታል:: ቀል ነህ ልበል?» ብሎ ጓደኛው ቢያፌዝበት፣

«ትእዛዙን እርሳው፣ ቡናውን ተወው» በማለት ስህተቱን ወዲያውኑ አረመ::


* * *

## ውጪ ለመውጣት

«እማምዬ፣ ውጪ ወጥቼ ጴጥሮስ ጋር ልጫወት?»

«አይ፣ ጴጥሮስ መጥፎ ልጅ ነው፤ አርፈህ ብትቀመጥ ይሻላል::»

«እንግዲያው ወጥቼ ልደብድበዋ!»





## ሙያ ያስፈልጋል

ጋብሮቮው አናጢ በእንጨት የተሰሩ የሚያማምሩ የቤት ዕቃዎች ሊሸጥ ኤሊና ከተባለችው ከተማ ወርዶ ሳለ፣ ቶርባጂ - ማለትም ሀብታም ሰው - ዕቃዎቹን ከመረመረ በኋላ ዋጋቸውን ይጠይቀዋል::

ከዚያም፣ «የምትጠይቀው ዋጋ ዕቃዎቹን ከብር የሰራሃቸው እንጂ ከእንጨት የሰራሃቸው አያስመስልም» በማለት ቶርባጂው ቢለክፈው፣

«ስማ! እንጨት እንደሆነ በሽበሽ ነው:: ከወዲያ ማዶ ካለው ጫካ ውስጥ ገብተህ የተለያዩ ዕቃዎችን መሥሪያ እንጨት ልታገኝ ትችላለህና ራስህ ሞክረዋ!» ሲል መለሰለት::

* * *

## ማዕበሉ ብቻ ይለፍ

ጋብሮቮውና ልጁ ጀልባቸውን እየቀዘፉ ሲዝናኑ ከፍተኛ ማዕበል ይነሳል:: ማዕበሉ ጀልባይቱን ሽቅብ አጉኖ ቁልቁል ሲመልሳት የተመለከተው አባትም በሁኔታው ተደናግጠ «አምላኬ ሆይ! ከዚህ መከራ ካወጣኸኝ የጀልባዬን ተራዳ የሚያክል ሻማ አበራልሃለሁ» ሲል ይሳላል::

በፍራቻ ተውጦ ጭብጥ ብሎ ተቀምጦ የነበረው ልጁ ይህን ሲሰማ ተገርሞ፣ «አባዬ! ሻማ ሰሪዎች ተራዳ

የሚያክል ሻማ ይሰራሉ አንዴ?» በማለት ቢጠይቀው፣

«አፍህን ዝጋ አንተ ክልፍልፍ! ማዕበሉ ብቻ ይለፍ እንጂ ሌላውን በኋላ እናስብበታለን» አለው ይባላል።

* * *

## ጥሩ ጓደኛ

በጫወታቸው የተፋቀሩት ሁለት የስኮትላንድና የጋብሮቮ ተወላጆች ከእለታት አንድ ቀን ውይይት የሚካሄድበት አንድ አዳራሽ ይገባሉ። ውይይቱ እንዳበቃም አዘጋጆቹ ገንዘብ የመሰብሰብ እቅድ እንዳላቸው ያስታውቃሉ።

ወዲያውኑ የእስኮትላንዱ ተወላጅ ሕሊናውን ስቶ ወደቀ። ጋብሮቮውም ጓደኛውን ደግፎ ካዳራሹ ወጣ።

* * *

## የመርሳት ጉዳይ

«ዘበኛ፣ ዕቃዎቼን በሙሉ መኪናዬ ላይ ጭነህልኛል?»

«አዎን ጌታዬ።»

«ምንም እንዳልረሳሁ እርግጠኛ ነህ?»

«አዎን፣ ምንም አልረሳሁም ጌታዬ - ከጉርሻዬ በስተቀር።»

* * *



## ጋብሮቮዊ መስተንግዶ

«አንዱን ቀን ጋብሮቮ ብቅ ብትል ጐረቤቶቼ ዘንድ ጋብዤህ ምን ያክል እንግዳ ተቀባይ ሕዝብ እንደሆንን አይተህ ትሄድ ነበር» አለ አንዱ ጋብሮቮ ወዳጁን ሲጋብዝ።

* * *

## እያሰሉ ነው

ጋብሮቮው ጓደኛው ቤት ግብዣ ተጠርቶ ይሄዳል። ጥቂት አረፍ እንዳለም በስተቀኙ ተቀምጦ ለነበረው ሰው ሲጋራ ይጋብዛል።

«አላጤስም ወዳጄ። ስላሳብህ አመሰግናለሁ» በማለት ተጋባዡ ይመልሳል። ከዚያም ጋብሮቮው ከበስተግራው ተቀምጦ ወደነበረው ሰው ዞሮ ብሎ ፓኬቱን ያቀርብለታል።

«እኔም አላጤስም፣ አመሰግናለሁ» ሲል ሁለተኛውም ገላገለው።

ይኸኔ ሚስቱ በሹክሹክታ «ጋባዦችንንስ ለምን አትጋብዘውም?» በማለት የተግሳፅ ጥያቄ ብታቀርብለት፣

«እሱማ እንደሚያጨስ አውቃለሁ!» ሲል ከሷ ዝቅ ባለ ሹክሹክታ መለሰላት።

* * *

## እውነቱን ተናግሮ እመሸበት የድሯል

አንዱ ተሳፋሪ ፌርማታ (አውቶቡስ መቆሚያ) ሲደርስ ይወርድና አውቶቡሱ ሊነሳ ሲል ፈጥኖ ይሳፈራል። እንዲህ እያለ ብዙ ፌርማታ ሲያልፍ ያስተዋለ አንድ ተሳፋሪ በነገሩ ተገርሞ ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ቢጠይቀው፣

«ምናልባት ተቆጣጣሪ ከመጣ አሁን ገና ነው የተሳፈርኩት ለማለት እንዲያመቸኝ ብዬ ነው» ሲል ጋብሮቮው መለሰለት።

* * *

## ትዝብት

ጋብሮቮዎች ታዋቂውን ሕዝባዊ አርቲስት ፃንኮ ላቭሬኖቭን ከተማቸውን እንዲጐበኝና ጥንታዊ የሆኑትን አካባቢዎች እንዲስልላቸው ይጋብዙታል።

ታዲያ በግብዣው የተገረሙ ጓደኞቹ «ከሌሎቹ አርቲስቶች በምን ብትበልጥ ነው አንተን መርጠው የጋበዙህ?» እያሉ ቢጠይቁት፣

«ሥራው በርካሽ እንዲጠናቀቅላቸው ፈልገው ነው፣ ወዳጆቼ። እኔ እንደምታውቁት አላጤስም፤ አልጠጣም፤ እህል የምበላውም በቀን አንዴ ብቻ ነው» ብሎ ምስጢሩን ገለፀላቸው።

* * *



## ጥቅም ባይኖረውም

ጋብሮቮው ከዚህ ዓለም በሞት ይለይና ንብረቱ ሲታይ ለዕቃዎቹ ዝርዝር አዘጋጅቶላቸው በሥርዓት ተቀምጠው ይገኛሉ።

ለአብነት ያህል፣ ከመሳቢያዎቹ ባንዱ ውስጥ የተገኘው ብጥስጣሽ ክርና ሲባጐ የሞላ ከረጢት ላይ የተፃፈው ማስረጃ «ጥቅም የሌላቸው የክር ቁርጥራጮች» የሚል ነበር።

* * *


## «...እና የልጁ»

አባቱ የሞተበት ጋብሮቮ አቅሙ የሚፈቅድለትን መለስተኛ ሐውልት አሰርቶ «የቫሲል ቶንኮቭ መካነ መቃብር» የሚል አስፅፎበት ሲኖር ሳለ፣ አንድ ቀን በሌላ ሰው ቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ሊገኝ ወደዚያው ስፍራ ይሄድና እንዳጋጣሚ ልብ ድካሙ ተነስቶበት አባቱ መቃብር አጠገብ ይወድቃል። ይኸኔ የሕይወቱ ፍፃሜ መድረሱን የተረዳው ጋብሮቮ ወደ አባቱ መቃብር በሆዱ እየተሳበ ሄዶ፣ «የቫሲል ቶንኮቭ መካነ መቃብር» የሚለው ፅሁፍ ስር «...እና የልጁ የቶንኮ» የሚል ጨመረበት።

* * *

# እግዜርን ማቄል

አንዱ ገጠሬ ከአያ ሚንዮ ብድር ይጠይቅና ብዙ ከተከራከሩ በኋላ ዘጠኝ በመቶ ወለድ ሊከፍል ተስማምቶ ውሉ እየተረቀቀ ሳለ ገጠሬው «ይህ አይነት ውል ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ:: አያ ሚንዮ ዘጠኝ በመቶ ወለድ ሲያስከፍሉ እግዜርን እንኳን አይፈሩም?» ቢላቸው «ምን ያስፈራኛል ወዳጄ? እግዜሩ ዘቅዝቆ ከላይ ወደታች ሲመለከት ዘጠኝዋ ስድስት ስለምትመስለው የሚያቀያይመን ነገር አይኖርም» አሉት::





# ጋብሮቮዎች፤

...ሁለት ሳንቲም ከጠፋባቸው እሱን ፍለጋ የዐሥር ሳንቲም ሻማ ያቃጥላሉ:: ይህንም የሚያደርጉት እያንዳንዷ ስባራ ሳንቲም በከንቱ አለመባከኗን ስለማረጋገጥ ያላቸው ጽኑ እምነት እንዳይላላ ሲሉ ነው::

...ዘመድ ጥየቃ ሲሄዱ ለራሳቸው የሚሆን ምግብ በሳህን ይዘው ይሄዳሉ:: የጊዮርጊስ ዕለት ግን ራት የሚበሉት ባንድነት ነው:: ሆኖም ሁሉም የሚበሉት የየራሳቸውን የግልገል አሮስቶ ነው::

...አዲስ ነገር መሥራቱ ወይም አዲስ ዘዴ መገኘቱ በሌላ አገር ከተወራ ጋብሮቮዎቹ ዘንድ ያረጀ ያፈጀ ጉዳይ ነው ማለት ነው::

...ዶሮ የሚገዙት ሩቅ አገር ሄደው ነው:: ምክንያቱም እያንዳንዱን የባቡር ማለፊያ ዋሻ ጭለማ አቋርጠው ባለፉ ቁጥር ዶሮዎቹ የነጋ ስለሚመስላቸው ዕንቁላል ይጥላሉና::

...እመኖሪያ ቤታቸው ሦስት ዐይነት ቡና ያስቀምጣሉ:: ንጽሑ ቡና ላይ «ሀ»፣ ገብሱ ላይ «ለ» እና ከትርፍራፊ የቡና ጭላጭ ተጠራቅሞ የደረቀው ላይ «ሐ» ብለው ይጽፉናም እንግዳ ሲመጣ እንደፍቅሩ ፅናት ቡና ተፈልቶ ይስተናገዳል::

* * *

## «አይሞትም»

አንድ ሀብታም ጋብሮቮ ጣር ይይዛቸውና ልጃቸው የንስሐ አባታቸውን እንዲጠራላቸው ያዙታል፡፡ ሆኖም ለልጅየው የንስሐ አባትየው መምጣት አስፈላጊነት ስላልታየው፤ «እሺ እሄዳለሁ» እያለ ሳይሄድ ቆየ፡፡ በመጨረሻ ግን አባትየው አምርረው ስለተናገሩት እያጉተመተመ ወደ ቄሱ ዘንድ ሄደ፡፡

ልጅየው ከተላከ ብዙ ጊዜ ማለፉን የተገነዘቡት ቄስ፣ «ታዲያ ሽማግሌው'ኮ እስካሁን ሞተው ይሆናል» ሲሉ ተቆጡት፡፡

«ኧረ አያስቡ አባቴ እርስዎ እስኪደርሱ ድረስ እንደማይሞት እርግጠኛ ነኝ፡፡ ምክንያቱም እንደመጡ ያለብዎትን የመቶ ሌቭ ብድር እንደሚከፍሉት አረጋግጬለታለሁ» አላቸው፡፡

* * *

## የብረቱ ሣጥን

አያ ሚንዮን አገሬው ሁሉ የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው ቢሆንም፣ ለንብረታቸው ቀናዒ በመሆናቸው ብዙ ሰዎች ያሽሟጥጧቸውና ይሥቁባቸው ነበር፡፡

አያ ሚንዮ ግን፣ «ማንኛውም ካዝና (የብረት ሣጥን)



ለያዘው ንብረት ቀናዒ አይደለምን? አሊያ እንዴት በጥንቃቄና በክብር ሊያቆየው ይችላል?» በማለት በርጋታ ይመልሱ ነበር፡፡

* * *

## የደሞዝ ጭማሪ

ጋብሮቮው ሥራ ሊቀጠር ይሄድና ክፍያው ስንት እንደሆነ ይጠይቃል፡፡

«መነሻ ሰባ ሌቭ እንከፍልሃለን፡፡ ጥቂት ጊዜ ከቆየህ ደግሞ እስከ መቶ ሌቭ መድረስ ትችላለህ፡፡»

«መልካም፤ እንግዲያው ጥቂት ቆይቼ እመለሳለሁ፡፡»

* * *

## ብልህ ነጋዴ ለመሆን

ከጋብሮቮ ሱቅ ዕቃ ሊገዛ ጐራ ያለ አንድ እንግዳ «ጋብሮቮዎች እንዴት ጉበዝ ነጋዴዎች ሊሆኑ ቻሉ?» ሲል ባለቤቱን ይጠይቀዋል፡፡

«ብዙ ዓሣ ስለምንበላ መሆን አለበት፡፡»

እንግዲያው ይህን ልዩ ዐይነት ዓሣ ሽጥልኝ ብሎ ውድ በሆነ ዋጋ ገዝቶ ሔደ፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ እሱቁ ይመለስና፡ «ዓሣውን በልቼዋለሁ፡፡ ቢሆንም ጋብሮቮ አልሆንኩም» በማለት ባለ

ሱቁን ሲያጫውተው፣

«ተጨማሪ ዓሣ መብላት አለብህ ማለት ነዋ» ሲል መለሰለት::

«ከበቀደሙ ዋጋ ከቀነስክልኝ ቅር አይለኝም» በማለት እንግዳው ሲንተባተብ፣ ጋብሮቮው ከልቡ ሥቆ፣ «ይኸውልህ ጋብሮቮ መሆን ጀምረሃል» አለው::

* * *

## ቁጠባ

ጋብሮቮው ከባቡር እንደወረደ ታክሲ ያስቆምና «ከተማው መኻል በስንት ታደርሰኛለህ?» ሲል ይጠይቀዋል::

«ሁለት ሌቫ ብቻ ነው፣ ይግቡ ጌታው» ብሎ ባለ ታክሲው በሩን ቢከፍትለት፣

«ግዴለም፣ አመሰግናለሁ:: በእግሬ ብሔድ ምን ያክል ገንዘብ እንደማድን ለማወቅ ነው የጠየቅኩህ» አለው::

* * *

## ፌጠራ

የአራዳ ልጆች «ቃሪያ ሱሪ» የሚሉትን እግረ ጠባቡን ሱሪ፣ «ሚኒ ስከርት» የተባሉ ጉርድ ቀሚሶችን፣ ባንድ በኩል ብቻ መጫሪያ ያላቸው የክብሪት ሣጥኖችንና



የመሳሰሉትን ሁሉ የፈለሰፉት ጋብሮቮዎች ናቸው ይባላል::

* * *

## ባቡር ላይ

ቲኬት ቆራጩ ትንሹን ልጅ «ስንተኛ ክፍል ነህ» ሲል ይጠይቀዋል::

«ሦስተኛ::»

«ዕድሜህስ ስንት ነው?»

«አምስት» አለ ጋብሮቮው ሕፃን - የመሣፈሪያውን ዕድሜ ገደብ ለማስታወስ ጥቂት ካሰበ በኋላ::



## የጋብሮቮው ነጋዴ ኑዛዜ

«...በብዙ ችግር የተካበተ ሀብት ነው። ጥሬ ብሩን ማፍራት ከባድ ፈተና ነበር፤ የተካበተውን ማስቀመጡም ከፍተኛ መከራ ነበር። ባጭሩ ይህን ንብረት ሁሉ ማፍራቱና ማኖሩ እጅግ መራራ ተግባር ነበር።»

* * *

## ሰበብ

ሕፃኑ ጋብሮቮ ከተማሪ ቤት ቀርቶ ኖሮ በማግስቱ ክፍል ሲገባ አስተማሪው ለምን እንደቀረ ይጠይቁታል።

«እማዬ ሱሪዬን ስላጠበችው የምለብሰው አጥቼ ነው የቀረሁት ቲቸር» ብሎ ችግሩን ይገልፅና ይቅርታ ተደርጉለት ይገባል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ በድጋሚ ይቀራል። በዚህን ጊዜ አስተማሪው ተቆጥተው፣

«አንተ ልጅ አላበዛኸውም? ትላንት ደሞ ለምን ቀረህ?» ቢሉት፣

«ከቤት ስመጣ የርስዎን ቦላሌ ሽቦ ላይ ተሰጥቶ ስላየሁት ወደቤቴ ተመለስኩ እንጂ ወደ ትምህርት ቤት እየመጣሁ ነበር» ሲል መለሰላቸው።

* * *



## እንዴት ጠብታ ላለማባከን

ጋብሮቮው ጠርሙስ ፈለገና በስንት መከራ አንዲት ጠርሙስ ቢያገኝ እርሷም ጭላጭ አዮዲን ይዛለች (አዮዲን አዲስ ቁስል ላይ የሚቀባ መድኃኒት ነው)። ታዲያ ጋብሮቮው አዮዲኗን ማባከን ትክክል መስሎ ስላልታየው ጣቱን ቆርጦ አዮዲኗን ከተቀባ በኋላ ጠርሙሷን ለጉዳዩ አዋላት።

* * *

## «የጥንት ማር»

ጋብሮቮው ጎረቤቶቹን ሊጠይቅ ይሄድና ማር ይጋበዛል። ሆኖም የቀረበለት ማር ጣዕመ ቢስና ውሃ የበዛበት ነበር። አጅሬ ቢቀምሰው፣ ቢያጣጥመው አልጣፍጥህ አለው። ይኸኔ እየሳቀ «ይህ ማር ጥንት ንቦች ማር መሥራት ይለማመዱ በነበረበት ወቅት የሰሩት መሆን አለበት» ሲል አሸሟጠጣቸው።

* * *

## ማን ያውቃል?

ጋብሮቮው ቤቱ ቢሄድ አንዳገር ውጫሎች በሩ ላይ ሲጫወቱ ያያል። ጥቂት ካሰበ በኋላም «እዚህ ምን ታደርጋላችሁ ልጆች? እዚያ ማዶ የምታዩትን ጋሪ የሚገፋው ሰውዬ ፍራፍሬ በነፃ እያደለ ነው» ይላቸዋል።

ጨዋታው ሮዲያውኑ ፈረሰ። ልጆቹም ወደጋሪው እየተሯሯጡ ሄዱ። ጋብሮቮው በረንዳው ላይ ቆሞ ብሎ ሲመለከት ግን ብዙ ሰው ጋሪውን ከቦት እንደቆመ አየና፣ «እውነት ፍራፍሬ በነፃ እየሰጡ ይሆን እንዴ?» ብሎ እየሮጠ ወደጋሪው ሄደ።

* * *

## የቆዳ ዕዳ

ጋብሮቮው የሚስቱን ጉሮሮ ለማስቧጠጥ ሐኪም ዘንድ ይዟት ይሄዳል። ሐኪሙም ወይዘሮዋን አፕራሲዮን ካደረጉ በኋላ፣ «ይህን ቶንሲል ባለቤትህ ገና ሕፃን ሳለች መቆረጥ ነበረበት» ቢሉት፣

«በጣም አመሰግናለሁ፣ ዶክተር። በልጅነቷ መወገድ ከነበረበት ደረሰኝ ይስጡኝ። የኦፕራሲዮኑን ሒሳብ ከአባቷ እቀበላለሁ» አላቸው ይባላል።

* * *

## የመጨረሻው ሒሳብ

ጋብሮቮው በጠና ስለታመመ ሐኪም ወደ ትውልድ አገሩ እንዲመለስ ያዘውና ባቡር ይሳፈራል። ግን የሞት ሞቱን በየጣቢያው እየወረደ እስከሚቀጥለው ጣቢያ ድረስ ብቻ ቲኬት ያስቆርጥ ነበር። ተሳፋሪዎቹ በዚህ እንግዳ ትግባር ተገርመው ለምን ቀጥታ ጋብሮቮ የሚያደርስህን ቲኬት አንዴ አታስቆርጥም?» ብለው ቢጠይቁት፣



«አገሬ ሳልደርስ መንገድ ልሞት ስችል ለምን ገንዘቤን በከንቱ አባክናለሁ?» ብሎ መለሰላቸው።

* * *

## ተደጋጋሚ ሒሳብ

አንዱ ጋብሮቮ ምግብ ቤት ውስጥ ነው። ጥግ የተቀመጠው ተስተናጋጅ ተኝቷል። አንዱ አሳላፊ ሌላውን «ይህን ሰው ለምን አታስወጣውም? አስሬ ከእንቅልፉ ትቀስቅሰዋለህ፤ እሱ ግን ተመልሶ ይተኛል» ይለዋል።

«ለምን አስወጣዋለሁ? በቀሰቀስኩት ቁጥር ሒሳቡን ጠይቆኝ ያላንዳች ክርክር ይከፍላል።»

* * *

## አዲሱና አሮጌው ዘመን

ወጣቱ ጋብሮቮ አያቱን «አባቢ! ባያቱ ስም ለሚጠራ ልጅ መኪና ገዝቶ መሸለም ባሁኑ ዘመን ፋሽን ሆኗል» ቢላቸው፣

«ታዲያ እኔ የቀድሞው ዘመን ፋሽን ተከታይ ነኝኮ ልጄ» አሉት ይባላል።

* * *

## ለጋሥነት

«አባዬ ትላንትና ማታ በሕልሜ የአምስት ሌቭ

ቸኮላታ ስትገዛልኝ አየሁ።»

«ጣባይህን ካሳመርክ ደሞ በዘመን መለወጫ ሕልምህ አንድ ኪሎ ሙሉ ቸኮላታ እገዛልሃለሁ።»

* * *

## ምንም ሳይኖር

አባት «እንካ ሁለት ሌቭ፣ ዳቦ ቤት ሒደህ ለሁለታችንም አንዳንድ ዳቦ ገዝተህልን ና» ብሎ ልጁን ይልካል። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሕፃኑ ጋንቸ የራሱን ዳቦ እየገመጠ ልታልቅ ስትል ይመለሳል።

«ያንተ ሌቭ ተመልሶልሃል፣ አባዬ። ዳቦ ሻጬ አንዲት ዳቦ ብቻ ነበረች የቀረችው።»

* * *

## ከባድ ውለታ

የቤቱን ዙሪያ ብቻውን ማጠር እንዳልቻለ የተመለከተ የጐረቤት ሰው ጋብሮቮውን ያግዘዋል።

ቀኑን ሙሉ አብሮት ሲሰራ ዋለናም አመሻሹ ላይ ሥራው ተጠናቀቀ። ይኼኔ ጋብሮቮው ቴታው ላይ እጆቹን እየጠራረገ «እግዜር ይባርክህ ወዳጄ። ስላደረግህልኝ እርዳታ ከልብ አመሰግንሃለሁ። በከንቱ የደከምህም እንዳይመስልህ። ከልብ የመነጨ ምርቃት ከገንዘብ ይበልጣል» ብሎ አሰናበተው።

* * *



## ሸክምና ክብደት

የተኩስ ልምምድ ከተደረገ በኋላ ሁለት ወታደሮች ዒላማዎቹን እንዲያመጡ ተልከው ይሄዳሉ። እዚያም እንደደረሱ አንዱ ወታደር ቀዳዳዎቹን በጥንቃቄ መቁጠር ጀመረ።

«ምንድነው የምትሰራው ጃል?» ብሎ ባልደረባው ቢጠይቀው አንዱን ዒላማ እየተሸከመ «ብዙ ቦታ የተበሳሳውን ዒላማ ለመምረጥ ነው። ክብደቱ ቀለል እንዲልልኝ» ሲል ጋብሮቮው መለሰለት።

* * *

## ዜና እረፍት

ጋብሮቮው በአባቱ ቀብር እለት እሱቁ ላይ የለጠፈው ማስታወቂያ፡

«አባቴ በገበያ ቀን በመሞቱ እግዚአብሔር ይቀር ይበለው። ነፍሱ በላይኛው ቤት ትፅናናም ዘንድ ሱቁ እስከአመሻሹ ክፍት ሆኖ ይቆያል።»

* * *

## «መሽቷል ካሉማ...»

ወጣቱ ጋብሮቮ የግንበኝነት እውቀት ለመቅሰም ካንድ ግንበኛ ዘንድ ተቀጥሮ ይሰራ ነበር። ይሁንና ሽማግሌው ተለማማጆቹን ከ[illegible] እስከ ምሽት ድረስ እንዲሰሩ

ያስገድዷቸው ስለነበረ ወጣቶቹን በጣም ይደክማቸው ነበር።

ታዲያ አንድ ቀን አመሻሹ ላይ ወጣቱ ጋብሮቮ ጮክ ብሎ ግድግዳ ላይ የምትሄደውን አይጥ ተመልክቱ ጋሼ?» ሲል ጠየቃቸው።

ሽማግሌውም «በጨለማ ዐይኔ አያይም ልጄ!» ብለውት ሥራቸውን ቀጠሉ።

«እርስዎ መሽቷል ካሉማ የእለቱ ሥራችን አብቅቷላ!» ብሎ ጋብሮቮው እንደተናገረም ወጣቶቹ በፍጥነት ቱታቸውን አወላልቀው ተፈተለኩ።

* * *

## የአባት ምክር

ጋብሮቮው ልጁን ሊጠይቀው ወደሶፊያ (ቡልጋሪያ ርእሰ ከተማ) ይሄዳል። ጥቂት እንደተጨዋወቱም ልጅየው «አባዬ! ዛሬ ጠዋት ሁለት ስቶቲንኪ አተረፍኩ። ይህም በአውቶቡስ ከመሳፈር ይልቅ ከአውቶቡስ ኋላ ኋላ በመሮጥ ለአውቶቡስ እከፍለው የነበረውን ገንዘብ በማዳኔ ነው» ብሎ ጉራውን መንፋት ሲጀመር፣

«አንተ ጅል! ከታክሲ ኋላ ሩጠህ ከሁለት ስቶቲንኪ የበለጠ አታተርፍም ኖሯል?» በማለት ገሰፀው።

* * *



## ቅሬታ

ቤት የመሥራት ውጥን የነበራቸው ጋብሮቮ ባልና ሚስት ምሳቸውን ይበላሉ። በትላልቅ የእንጨት ማንኪያ የባቄላ ሾርባቸውን እየዛቁ ሲጠጡም የልጅየው አባት ባጋጣሚ ይመጣሉ። እንዲበሉ ቢጋበዙም፣ «የባቄላ ሾርባ አካፋ በሚያክል ማንኪያ የምትውጡ ፍጡሮች እድሜ ልካችሁን ቤት አትሰሩም» ብለው አኩርፈው ሄዱ።

* * *

## የግማሽ ዋጋ ቲኬት

አውቶቡስ ላይ ነው። «ለኔና ለባለቤቴ ሁለት ቲኬቶች፣ ለልጄ ደግሞ የግማሽ ዋጋ ቲኬት ቁረጥልኝ» ሲል ጋብሮቮው



ቲኬት ቆራጩን ያዘዋል።

«ምን ማለትዎ ነው ጌታው? ይህኮ ሕፃን ልጅ አይደለም። አባቱን አክሏል። ሌላው ቢቀር የለበሰውን ቦላሌ ርዝመት ብቻ ይመልከቱት» ብሎ ተንጣጣበት።

«መልካም እንግዲያውስ ለልጁና ለኔ ሁለት ቲኬት ቁረጥልን። ባለቤቴ ግን የለበሰችው ጉርድ ቀሚስ ስለሆነ የግማሽ ዋጋ ቲኬት ቁረጥላት» አለው ጋብሮቮው ኮስተር ብሎ።

* * *

## በተስፋ መኖር

የሎተሪ አስተዳደር ጋብሮቮ አካባቢ ባደረገው ጥናት በየወሩ አንድ ጊዜ የሚወጣው የሎተሪ ቲኬት በሳምንት አንዴ ከሚወጣው ይልቅ በብዛት እንደሚሸጥ ይረዳል። የዚህን ምክንያት እንዲመረምሩ የሥነ ልቡና አዋቂዎችና ሶሲዮሎጂስቶች ቢመደቡም ምክንያቱን መረዳት ይሳናቸዋል። በመጨረሻ ጋብሮቮዎች ራሳቸው «በአንድ ወር የሚወጣውን ቲኬት ከቆረጥን ወሩን በሙሉ በተስፋ እናሳልፈዋለን። የሳምንቱን ከቆረጥን ግን ለረጅም ጊዜ በተስፋ ተንጠልጥለን አንኖርም» በማለት ምክንያቱን ገለፁላቸው።

* * *



## ሽንኩርት ብቻ

ገጠሬው ጋብሮቮ ሽንኩርት ጭኖ ወደገበያ ሲገሰግስ አህያዪቱ ከተማው አካባቢ ስትደርስ ለገመችበት፣ አልንቀሳቀስ አለች። ይኸኔ ገበሬው ተቆጥቶ አህያዪቱን ይቀጠቅጣት ጀመር።

ድርጊቱ የሰቀጠጠው አንድ መንገደኛም «ሰውዬ ሕሊና የለህም?» ብሎ ቢጮህበት፣

«እሱንስ ጨርሻለሁ ጌታዬ። አሁን ያለኝ ሽንኩርት ብቻ ነው» አለው ይባላል።

* * *

## ዝና

ሰዎች ስለ ጋብሮቮዎች የሚወሩትን ቀልዶች እያነሱ 'ይኸ ስለ እናንተ የተወራ አይደለም? ይኸስ? እያሉ ቢቀልዱበት ጋብሮቮው «በርግጥ ስለኛ የተወራ ነው። ብዙ የሚወራውኮ ዝነኛ ስለሆኑ ሰዎች ብቻ ነው» ሲል መለሰላቸው።

* * *

## ጋብሮቮዎች

...የሺፕካን ሰርጥን ሲያቋርጡ ጫማቸው እንዳያልቅባቸው የተራራ መውጪያ ጫማ ይከራያሉ ይባላል።

...የቤት ቁሳቁሳቸው ብዙውን ጊዜ የሚሰራው ከእንጨት ነው - የሸክላ ዕቃዎች አምስት ዓመት ያህል ሳይሰበሩ ሊያገለግሉ አይችሉምና::

...ቄስ ሚንዮ የሚያበስሉት ሾርባ እጅግ ከመቅጠኑ የተነሳ፣ ዝንቦች እንኳን ሊያርፉበት ይፀየፋሉ ይባላል::

...በብዙ ጨው ታሽቶ የተጠበሰ ዓሣ መብላት ያዘወትራሉ፤ ጥቂት በልተው ብዙ ውሃ በመጠጣት ሆዳቸው ይሞላ ዘንድ::

...ሲኒማ ቤት ሲገቡ የሦስተኛ ማዕረግ ቲኬት ይቆርጡና መብራቱ ሲጠፋ ወደ አንደኛ ማዕረግ ሰርገው ይገባሉ::

...አንደዜ ሰባት ጋብሮቮዎች አንዷ.ት ማንኪያ እየተቀባበሉ ሾርባ ሲጠጡ ሌባ ባጠገባቸው ማለፉን ያየ አልነበረም - የሁሉም ዐይን ማንኪያዋ ላይ ነበረና::

...የጋብሮቮን የቤት እመቤቶች አሮጌ ሸሚዝ አይለያቸውም ይባላል:: ምክንያቱም የጠረጴዛ ጨርቃቸውን በመስኮት በኩል ሲያራግፉ ጐረቤቶቻቸው ከሩቅ አይተው «ለካስ ሠራተኛ አላቸው!» በማለት እንዲያደንቋቸው ስለሚፈልጉ ነው::

...ለሚስቶቻቸው ጋውደር ሲገዙ ከፊሉን በሌላ ዕቃ ቀንሰው የእህል ዱቄት ይሞሉበታል - ለብዙ ጊዜ ያገለግላቸው ዘንድ::

...ሙቀትና ወበቅ በሚበዛበት ወራት የፊት ማራገቢያ



ፋሽን በነበረበት ዘመን ጋብሮቮዎች ማራገቢያውን ከማወዛወዝ ይልቅ ጭንቅላታቸውን ማወዛወዝ ይመርጡ ነበር:: ለምን? ማራገቢያው ቶሎ እንዳያልቅባቸው ነዋ!

* * *

## ለጋሱ ከንቲባ

ብዙዎቹ የከተማ ነዋሪዎች የሚሰበሰቡባቸውን መጠጥ ቤቶች የሚያዘወትር አንድ ከንቲባ ነበር:: ታዲያ ገና ገብቶ ከመቀመጡ ነዋሪዎቹ በግብዣ ያጣድፉታል:: እያንዳንዱ ነዋሪ ካልተጋበዝክልኝ እያለ ያስጨንቀዋል:: ከንቲባውም የገዙለትን በሙሉ ባይጠጣም ግብዣቸውን ይቀበላል:: የተጋበዘው መጠጥ ጠርቀምቀም እንዳለለትም ጮክ ብሎ፣ «ከበር መልስ አንዳንድ ብርጭቆ በኔ ሒሳብ ተጋብዛችኋል!» በማለት ያንበሸብሻቸዋል::

* * *

## ፍቱኑ መድኃኒት

የእግር ላይ መጅ በማከም የታወቀ ጋብሮቮ ነበር:: እጅግ ዝነኛ ከመሆኑ የተነሳ በሽተኞች ከሩቅ አገር እየመጡ ይጐበኙት ነበር:: በርግጥም መድኃኒቱ ፍቱን ነበር:: ጋብሮቮው ምርመራውን እንዳጠናቀቀ እጁን እያሻሸ ክፍያ እንደሚጠብቅ ምልክት ያሳያል:: ሒሳቡን ከተቀለ በኋላም፣ «የሚደላ ጫማ ይግዙ!» በማለት ፍቱኑን መድኃኒት

ያገባቸዋል::

* * *

## «አይገርማችሁም?»

ጋብሮቮዋ ቤት እንግዶች ይመጡና ቂጣ ታቀርብላቸዋለች:: እንግዶቹም አንደኛውን ቂጣ ወዲያውኑ ጨረሱት:: አፈረችና ሁለተኛ ጋግራ ብትሰጣቸው እሱንም ጨርሰው ዐይናቸውን ማቁለጭለጭ ጀመሩ:: ሁናቴው ያላማራት ሴትዮ በመገረም እያጨበጨበች «አይገርማችሁም? ልክ እናንተ ስትጠግቡ ዱቄቱም አለቀ!» አለቻቸው::

* * *


## «ዘዴ ፈልግለት»

አንድ ቀን አያ ሚንዮ አንዱ ጋብሮቮ ልብስ ሰፊ ዘንድ ሄደው ልምምጥ ጀመሩ፤ «አየህ ኢቫን እጅግ የታወቅህ ባለሙያ መሆንክን ስለማውቅ ነው ወዳንተ የመጣሁት:: በዚህም ላይ የረጅም ጊዜ ደንበኛህ ነኝ:: ስለዚህ አሁን የምጠይቅህን እምቢ እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ኮቴን ገልብጠህ ስፋልኝ:: እንደምታየው ደግሞ ጨርቁ ገና አዲስ ነው::»



«ግን'ኮ ከዚህ ቀደም አስገልብጠውታል አያ ሚንዮ!»

«አዎን አስታውሳለሁ፤ በሚገባ አስታውሳለሁ እንጂ:: ሆኖም አንተ ባለሙያ ስለሆንክ ዘዴ አታጣም ብዬ ነው::»



## ጠቃሚ ምክር ለእንግዶች

ጋብሮቮዎቹን ሊጠይቋቸው የመጡት እንግዶች ካሁን አሁን ይሄዳሉ እያሉ ቢጠብቋቸው የማይሄዱ ሆኑ:: ምሽቱ እየገፋ በመሄዱና የፋኖሱ ጋዝ በመባከኑ የተከፋችው ጋብሮቫዊት «እንግዶቻችን ስለመሸባቸው መሄድ ይፈልጉ ይሆናልና ለምን አንተኛም?» አለችው ባለቤቷን::

* * *

## ምስጢር

እንዴት ባጭር ጊዜ ዝነኛ የዕደ ጥበብ አዋቂ ሊሆን እንደቻለ ለቀረበለት ጥያቄ ጋብሮቮው ሲመልስ «ነገሩ ቀላል ነው:: ጠዋት ተነስታችሁ ፊታችሁን ከታጠባችሁ በኋላ የምታደርቁበት ፎጣ ደረቅና ማንም ሰው ቀድሞአችሁ ያልተጠቀመበት መሆኑን አረጋግጡ» ብሏል::

* * *

## ማነቃቂያ

ጋብሮቮው ልጆቹ ሥራ ወዳድና በማለዳ እየተነሱ በርትተው ሥራቸውን የሚያግድፉ እንዲሆኑ ለማድረግ የተጠቀመበትን ዘዴ ተጠይቆ ሲያብራራ «በውነቱ ይህም አዳጋች አልነበረም:: ለአምስቱም ልጆቼ አንድ ጥንድ ጫማ አስቀምጥላቸውና ከሁሉም ቀድሞ የተነሳው ይጠቀምበታል:: አራቱ በባዶ እግራቸው ሲሰሩ አንዱ ብቻ ተጫምቶ ይሰራል ማለት ነው» ሲል ፈገግ ብሎ መልሷል::

* * *

## ከፍተኛ ምቾት

የጋብሮቮ መንገዶች ከመጥበባቸው የተነሣ ሰዎች በቀላሉ ሊተላለፉባቸው አይችሉም:: ስለዚህም ነው ጋብሮቮዎች «እስካልፍ ጠብቀኝ» ጉዳናዎች የሚሏቸው:: ቢሆንም መንገዶቹ ጠቀሜታም አላቸው:: ይኸውም




ከመንገዱ ዳርቻ የተሠሩት ቤቶች ጣሪያዎች ስለሚገጥሙ፤ በክረምት ወራት ያለዣንጥላ ጋብሮቮን መዘዋወር ይቻላል:: ፈረሶች ቢደነብሩም ከፊታቸው ባሉ ሁለት ሰዎች በቀላሉ ሊያዙ ይችላሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ጠላ ሻጮች በማለዳ አንዱ ጠርዝ ቆመው ግራና ቀኝ ለሚተላለፉ መንገደኞች ጠላ ይሸጣሉ:: የጋብሮቮ የቤት እመቤቶችም ዕቃ በሚዋዋሱበት ወቅት ዕቃዎቹን በመስኮት ነው የሚቀባበሉት::

* * *

## ፈረስን ለማበረታታት

ጋብሮቮ ነጋዴዎች ፈረሶቻቸው ዳገት በቀላሉ እንዲወጡላቸው ሲፈልጉ፤ በክረጢት ገብስ ይሞሉና ከፊት ለፊታቸው በዱላ ያንጠለጥሉታል:: ፈረሱም ያንን ገብስ ካሁን አሁን ደረስኩበት እያለ አንገቱን አስግጎ ዳገቱን ባንዳፍታ ይወጣዋል::



## ነቢይ

«እማምዬ፤ በሚመጣው ሳምንት አዲስ ሱሪ ይገዛልኛል፡ አይደል?»

«እንዴት ዐወቅህ?»

«የአባዬ ሱሪ ስለተቀደደ ነዋ።»

* * *

## «እንዳይሰማ»

ጋብሮቮው አንዳገር ጆንያ ጭኖ ወደ ገበያ ይሄዳል። ኮሳሳ ፈረሱ የጭነት ጋሪውን የሚጎትተው በጣር ነበር። ጥቂት ከተጓዘ በኋላ «ምን ጭነሃል፤ ጃል?» ሲል አንዱ መንገደኛ ጠየቀው።

«ገብስ ነው የያዝኩት» በማለት ጋብሮቮው አንሾካሾከ።

«ምን?»

«ገብስ» ሲል በድጋሚ አንሾካሾከ።

«ለምንድነው ታዲያ የምታንሾካሽከው? ጉሮሮህን አሞሃል ወይስ ሌላ ችግር አለብህ?»

«አይ ፈረሴን ሁልጊዜ የምቀልበው ገለባ ስለሆነ፣ ገብስ መጫኔን እንዳይሰማ ብዬ ነው።»

* * *



## በቅርቡ የተገኘውን

ጋብሮቮው ዶክተር ይሞታል። ታዲያ ባለቤቱ ለመቃብሩ የሚወጣውን ገንዘብ ለመቀነስ ስትል መኖሪያ ቤታቸው በር ላይ ይንጠለጠል የነበረውን፣ «ዶክተር ጋቫንኮቭ በሽተኞችን ከሦስት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ይመረምራሉ» የሚል ማስታወቂያ እንሥታ መቃብሩ ላይ አስለጠፈችው።

* * *

## ቅልጥፍና

ጋብሮቮው ለመስክ ሥራ ወጥቶ ሳለ ችግር ያጋጥመዋል። ይህንኑ ለአለቃው ማስታወቅ ስለነበረበትም፣ «የጉርፍ አደጋ ስለገጠመኝ የባቡሩ ጉዞ ለጊዜው ተቋርጧል። ምን ማድረግ ይገባኛል?» የሚል መልዕክት ይልካል።

አለቅየውም፣ «ከትላንት ጀምሮ ዓመት ፈቃድ ላይ ነህ» የሚል ቴሌግራም ላኩለት።

